የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

# ወደ ሮሜ ሰዎች

ክፍል አንድ

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| ክፍል አንድ | 3 |
| ክፍል ሁለት | 11 |
| ክፍል ሦስት | 16 |
| ክፍል አራት | 22 |
| ክፍል አምስት | 28 |
| ክፍል ስድስት | 35 |
| ክፍል ሰባት | 40 |
| ክፍል ስምንት | 45 |


# ክፍል አንድ

በሮም ከተማ ይኖሩ ለነበሩ አማኞች የተላከው "የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች" በመባል የሚታወቀው መፅሐፍ፥ የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት በተሟላ ሁኔታ የሚገኝበት እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል። ማርቲን ሉተር ወደ ሮሜ ሰዎች ስለተላከው መልእክት ሲናገር፥ "የአዲስ ኪዳን ዋና ክፍልና የተሟላ የወንጌል መልእክትን የያዘ ነው።" ("The chief part of the New Testament, and the perfect gospel.") ብሏል።

በዚህ የአዲስ ኪዳን መልእክት፥ ሐዋርያው ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ እንደ ኃጢአት፣ ፍርድ፣ እምነት፣ ጸጋ፣ ጽድቅ፣ ቅድስና ፣ የመንፈስ አሰራር፣ ህግ፣ ሥራ፣ የቤተክርስቲያንና የእስራኤል ሚና፣ የደህንነት እቅድ፣ ምርጫ፣ የአለም ታሪክ ዓላማ፣ የቅድስና መሰረታዊ መመሪያዎችንና የመሳሰሉ አንጋፋ መሪ ቃሎችን በማሰባሰብ የክርስትና ትምህርቶችን በተሟላ መልኩ አቅርቧል። የሮሜ መልእክት የሰዎችን ሕይወት በመለወጥና በቤተክርስቲያን ውስጥ ተገቢውን ለውጥ በማምጣት የእግዚአብሔር ኃይል በከፍተኛ ሁኔታ የሚገለጥበት መልእክት ነው።

ቅዱስ አውጉስቲን በመባል የሚጠሩ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ለአለማዊ ፍልስፍና ራሳቸውን ሰጥተው ከሚኖሩበት የላሸቀ ሕይወት የወጡት ለሮሜ ሰዎች የተፃፈውን ይህን መጽሐፍ ድንገት አንብበው እንደሆነ ታሪካቸው ያወሳል። አንድ ጊዜ በቤታቸው ሆነው ከደጅ ይጫወቱ ከነበሩ ልጆች መካከል አንደኛው፥ "አንስተህ አንብብ … አንስተህ አንብብ …" እያለ ሲጮኽ ሰሙ፤ እርሳቸውም በዚያ ሰዓት ባጋጣሚ ባጠገባቸው ተቀምጦ የነበረውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በማንሳት የሮሜን መልእክት አነበቡ። ከዚያም እንደ ቀድሞው ላይሆን ሕይወታቸው ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለወጠ ተብሎ ይነገራል።

በ18ኛው ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ጆን ዌስሊ የተሰኙ ሰው ከሮሜ ሰዎች መልእክት ሲሰበክ ሰምተው የሕይወታቸው አቅጣጫ በመለወጡ፥ የወንጌሉን ዜና ለአለም በማብሰርና ቃሉን በማስተማር ከፍተኛ ሥራ የሰሩ ሰው ሊሆኑ እንደቻሉም ይነገራል።

የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች፥ የእግዚአብሔር መንግስት ደጅ ለሰዎች በነጻ መከፈቱን በማብሰርና የእግዚአብሔርን መልካም አላማ በጥሩ ሁኔታ በመግለጽ የሰዎችን ሕይወት ዛሬም በከፍተኛ ሁኔታ እየለወጠ ይገኛል።

ይህ መልእክት ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መልእክቱን ከጻፈ በኋላ በ57 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ እንደተጻፈ ይገመታል። ስለዚህ ይህ መልእክት የተጻፈው ምናልባት ጳውሎስ በሦስተኛው የወንጌል ጉዞው ላይ እንዳለ ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጓዝ በሚዘጋጅበት ወቅት ላይ ሳይሆን አይቀርም የሚል እምነት አለ።

በቆሮንቶስ ወደብ አካባቢ ትኖር ስለነበረችው የክናክራኦሲ ፌበን መልካምነት መመስከሩና (ሮሜ 6፥1) የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነው ጋይዩስ እንዳስተናገደው መጥቀሱ (ሮሜ 16፥23) መልእክቱን በቆሮንቶስ ሳይፅፈው አይቀርም የሚለውን ሃሳብ በበለጠ ያጠናክሩታል።

ይህ መልእክት የተፃፈላቸው ሰዎች በሮም ቤተ ክርስቲያን ይገኙ የነበሩ ባብዛኛው ከአሕዛብ ወገን የነበሩ ክርስቲያኖች ነበሩ(ሮሜ 1፥7)። ሆኖም ግን በሮም ቤተክርስቲያን በሚገኙ ክርስቲያኖች መካከል ቁጥራቸው አነስተኛ ይሁን እንጂ አይሁዶችም ይገኙ እንደ ነበር ይገመታል። በሐዋርያት ሥራ ሁለት ላይ በተጠቀሰው የበዓለ ኀምሳ ቀን፥ "ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ ..." እንደመጡ (ሮሜ 2፥5)ከተጠቀሱት መካከል የሮም ሰዎች እንደነበሩ ተገልጿል(ሮሜ 2፥10)። ስለዚህ ምናልባት በሮም የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ኢየሩሳሌም ውስጥ ጌታን ተቀብለው በተመለሱ ሮማውያን ክርስቲያኖች እንደ ተመሰረተች ይገመታል።

የሮሜ መልእክት ምንም እንኳን በሮም ቤተ ክርስቲያን ለሚገኙ ክርስቲያኖች የተጻፈ ቢሆንም፥ ሮም በወቅቱ ይታወቅ ለነበረው አለም ዋና ከተማ ስለነበረች ፥ ይህ ጥልቅ መልእክት ያዘለ ደብዳቤ በቀላሉ ወደ ተቀሩት አለማት ሊሰራጭ የሚችል በመሆኑ፥ በመላው አለም ያሉ ክርስቲያኖችንም የሚመለከት ነበር ተብሎ ይታመናል።

ጳውሎስ በሮም ከሚገኙ ክርስቲያኖች ጋር በአካል ተገናኝቶ፥ "በእምነት እንዲፀኑ የሚያደርጋቸውን መንፈሳዊ ስጦታ ሊያካፍላቸው ..." ስለሚፈልግ ወደ ሮም መምጣት ይመኝ እንደነበር በመልዕክቱ መጀመሪያ ላይ ገልጿል። ስለዚህ ይህን መልእክት የጻፈው በሮም የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን ለመጎብኘት ዕቅድ ስለነበረው ተዘጋጅተው እንዲጠብቁትና የወንጌልን ይዘት ግልጽ ሊያደርግ ፈልጎ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይታመናል።

የሮሜ መልእክት ዋና ሐሳብ በምዕራፍ 1፥2-6 ላይ በምናገኘው "ወንጌል" በሚለው መሪ ቃል የተጠቃለለ ሃሳብ ሊሆን ይችላል። ሮሜ 1፥2-6 ላይ ጳውሎስ ስለ ወንጌል ይዘት በሚገልጽበት ጊዜ፥

1. ወንጌል የተስፋ ቃሉ ፍጻሜ ስለመሆኑ፣ (ቁ.2)
2. ወንጌል ስለሆነው አካል(ስለክርስቶስ) ማንነት (ቁ. 3)፣
3. ወንጌል ስለሚያሰገኘው ነገር (ቁ.5)
4. ስለ ወንጌል አላማ (ቁ.6) አብራርቷል።

ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን ለመጻፍ የተጠቀመበት ዘይቤ ልክ በችሎት ቀርቦ እንደሚሟገት አይነት ጥያቄ በማቅረብ ሲሆን መልእክቱ በሁለት መሰረታዊ መደብ ተከፍሎ መታየት ይችላል።



1. የመጀመሪያዎቹ አስራ አንድ ምዕራፎች የክርስትናን ትምሕርትን (አስተምህሮን)ያካተቱ ሲሆን፣

2. የተቀሩት አምስቱ ምዕራፎች ደግሞ የክርስትናን ትምህርት ተግባራዊ ትንታኔዎች ያካትታሉ።

## <u>የሮሜ መልእክት ማውጫ</u>

I. መግቢያ (1፥1-17)

- ሀ. ጳውሎስን በተመለከተ (1-5)
- ለ. በሮም ያሉትን ወገኖች በተመለከተ (6-15)
- ሐ. ወንጌልን በተመለከተ (16-17)

II. ጽድቅ በእምነት (1፥18-11፥36)

- ሀ. ኃጢአት - የደህንነት አስፈላጊነት
  1. ለአሕዛብ (1፥18-2፥16)
  2. ለአይሁድ (2፥17-3፥8)
  3. ለዓለም ሁሉ(3፥9-20)
- ለ. ጽድቅ በእምነት - የደህንነት መስፈርት
  1. በእምነት የሚሆን የእግዚአብሔር ጽድቅ (3፥21-31)
  2. የአብርሃም ምሳሌነት (4፥1-25)
- ሐ. ነጻነት- የደህንነት ውጤት
  1. ከቁጣ ነጻ (5፥1-21)
  2. ከኃጢአት ነጻ (6፥1-23)
  3. ከህግ ነጻ (7፥1-25)
  4. ከሞት ነጻ (8፥1-39)
- መ. አይሁድና አሕዛብ- የደህንነት ክልል
  1. እግዚአብሔር የሚያምኑትን ለማዳን መረጠ (9፥1-33)
  2. እስራኤል በራሷ ጽድቅ ለመታመን መረጠች (10፥1-21)
  3. አይሁድም ሆኑ አሕዛብ በእምነት ደህንነት ማግኘት ይችላሉ (11፥1-36)

III. የተለወጠ ሕይወት (12፥1-15፥13)

ሀ. አጠቃላይ ምግባርን በተመለከተ (12፥1-21)

ለ. የሕዝብ ባለስልጣናትን በተመለከተ (13፥1-7)

ሐ. ሌላን ሰው በተመለከተ (13:8-14)

መ. ደካማ ወንድምን በተመለከተ (14፥1-15፥13)

IV. መደምደሚያ አሳቦችና ቡራኬ 15፥14-16፥27)

**የክለሳ ጥያቄዎች፦**

1. የሮሜ መጽሐፍ ጸሐፊ ማነው? ለመልስዎ ምክንያትዎ ምንድን ነው?

በሮሜ 1፥1 ላይ እንደተገለጸውና ያጻጻፍ ዘይቤው እንደሚያመለክተው የሮሜ መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ሆኖም ግን ጤርጥዮስ የተባለ ሰው በጸሐፊነት እንዳገለገለው በሮሜ 16፥22 ላይ ተገልጾ እናገኛለን።

2. የሮሜ ሰዎች መልእክት ከየትና መቼ ነው የተጻፈው ይባላል?

3. ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈበት ምክንያት ምንድን ነው?

4. የሮሜ ሰዎች መልእክት ዋን ሐሳብ ምን ይመስልዎታል? በዚህ ጥናት ላይ የሮሜ መልእክት መሪ ሐሳብ የሚገኘው የት ነው ብለናል? በዚህ ይስማማሉ ወይስ ሌላ አመለካከት አለዎት?



5. ወደ ሮሜ ሰዎች መልእክት ዋና ሐሳብ "ወንጌል" በሚለው መሪ ቃል የተጠቃለለ እንደሆነ ቀደም ሲል አንስተናል (ሮሜ 1፥2-6 ፣ 16-17)። ለመሆኑ ወንጌል ስንል ምን ማለታችን ነው?

I. መግቢያ (1፥1-17)

ይህ የሮሜ መልእክት ጳውሎስ በሌሎች መልእክቶቹ ላይ ብዙ ጊዜ የሚጠቀምበትን የአጻጻፍ ዘይቤ የተከተለ ሲሆን፤ መልእክቱ የሚጀምረው ሰላምታና ምሥጋናን በማስተላለፍ ነው።

ሰላምታውንና ምሥጋናውን ተከትሎ በተለይ በመጀመሪያዎቹ አምስት ቁጥሮች ላይ ጳውሎስ ራሱን በተመለከተ አንዳንድ ጉዳዮችን ያነሳል።

6. ጳውሎስ፥ ሳኦል የሚለውን የእብራይስጥ ስሙን ትቶ ጳውሎስ የሚል የላቲን ስም የመረጠበት ምክንያት ምን ይመስልዎታል?

ጳውሎስን በተመለከተ (1-5)

7. በዚህ የመልእክቱ መግቢያ ላይ ጳውሎስ ስለራሱ የሚገልጻቸው አራት ነገሮች አሉ። እነዚህን ጳውሎስ ስለራሱ የሚገልጻቸውን አራት ነገሮች ከዘረዘሩ በኋላ ስለያንዳንዱ ሃሳብ ያለዎትን መረዳት ይግለጹ። (ሮሜ 1፥1-5)

## ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ (1፥1-2)

"ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ … "(ሮሜ 1፥1-2)

ጳውሎስ በሮም ትገኝ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወገኖች በጻፈው መልእክቱ በመጀመሪያ ላይ፥ በክርስቶስ "ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ" መሆኑን ይናገራል።

ሐዋርያ ማለት የተላከ ማለት ነው። ስለዚህ ሐዋርያ መልእክት አለው። ይህ ይዞ የሚቀርበው መልእክት ደግሞ ከላኪው ሥልጣንና ደረጃ አኳያ ሊታይ ስለሚገባ፥ መልእክቱ ያለምንም ጥያቄና ቸልተኝነት በስራ ላይ ሊውል የሚያስፈልገው ነው።

የክርስቶስ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ ደግሞ ከመልእክቱና ከተሰጠው ሃላፊነት በስተጀርባ የነገሥታት ንጉሥ ሥልጣንና ድጋፍ ስላለው፥ ሃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለው ተቀባይነትና ሥልጣን ሊኖረው ይገባል። በተጨማሪም፥ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች የጻፈውን መልእክት በምናጠናበት ወቅት፥ ስለ ሐዋርያ አንስተን እንደ ተነጋገርነው፥ ሐዋርያነት በራስ ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥሪ ብቻ የሚገኝ መሆኑን አይተናል። ስለዚህ አንድ ሰው ሐዋርያ ነኝ ስላለ ሐዋርያ ሊሆን አይችልም።

ሐዋርያ፦

- ጌታ ራሱ የላከው እንጂ በራሱ አነሳሽነት የሚሄድ አይደለም።
- ላኪው "አደራ" ብሎ የሰጠውን መልእክት እንጂ የራሱን መልእክት የሚያስተላልፍ አይደለም።
- የተሰጠውን መልእክት ለማድረስ የሚያስፈልገውን ብቃት ከላኪው የተቀበለ እንጂ በራሱ ብቃት የሚንቀሳቀስ አይደለም።

8. በዚህ ጉዳይ ላይ ምን አስተያየት አለዎት? ከዚህ ምን የሚማሩት ነገር አለ?

## የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ የሆነ (1፥1-2)

"… የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ ጳውሎስ …" (ሮሜ 1፥1-2)



ባርያ የሚለው ቃል አሽከር ወይም ሎሌ የሚለውን ቃል የሚያመለክት ነው። ባርያ ወይ ተገዝቶ ወይም በገዛ ፈቃዱ እራሱን የሰጠ ነው። ሮሜ በተጻፈበት ወቅት፥ በሮም ከስድሳ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ባሮች እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል። ስለዚህ ጳውሎስ ባርያ ነኝ ሲል በሮም የሚገኙት አንባቢዎቹ በቀላሉ ሊረዱት ይችሉ እንደነበረ መገመት ይቻላል።

በሮም የነበረው አይነት ባርንት ባይሆንም እንኳ፥ ሰዎች በዚህ ዘመንም ለተለያዩ ጌታዎች እንደሚገዙ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። እንዲያውም በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ መሰረት በጥቅሉ ሲገለጽ፥ በዚህ አለም ያሉ ሰዎች ሁሉ ባሮች ናቸው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ሰው ሁሉ አውቆም ሆነ ሳያውቅ የተገዛለት ጌታ አለው።

9. እስቲ ዛሬ በሰዎች ላይ ጌታ ሆነው ከሚገዟቸው ነገሮች መካከል እርስዎ የሚያውቋቸውን ይጥቀሱ?

በማቴዎስ 6፥24 መሰረት፥ገንዘብ በሰዎች ላይ ጌታ ሊሆን ከሚችሉ ነገሮች አንዱ እንደሆነ ተጠቅሷል።

10. ገንዘብ ሰውን ባርያ አድርጎ እንዴት ሊገዛ እንደሚችል ባጭሩ ይግለጹ። ገንዘብ በራሱ ኃጢአት ነው? ገንዘብ ጌታ ሆነ ሲባል ምን ማለት ነው?

በገላትያ 2፥4 እና 4፥3 መሰረት ደግሞ ሰው በአለም ከሚሰራጨው ትምሕርት ለሚያዳብረው አስተሳሰብ ባርያ ሊሆን ይችላል። በገላትያ 4፥9 ላይ እንደ ተገለጸው ይህ ባርንት ክርስቲያኖችም ወደ ባርንት ሊያስገባ የሚችል "ጌታ" ነው።

11. በገላትያ 4፥8 መሰረት ደግሞ በጥቅሉ ሰዎች ጌታ ላልሆኑ የተለያዩ ነገሮች ባርያ ሆነው ሊገዙ ይችላሉ። በእርስዎ ግምት እነዚህ በባሕርያቸው አማልክት ያልሆኑ፥ ነገር ግን ሰዎች የሚሰግዱላቸው ወይም የሚገዙላቸው ነገሮች ምን ምን ይመስሉዎታል?

ጳውሎስ ደማስቆ አቅራቢያ ላይ ባለ ስፍራ ድንገት መንፈሳዊው አይኑ ተከፍቶ ሊሰገድለት የሚገባውን ብቸኛና እውነተኛ ጌታ አየ። ስለዚህ ራሱን በፈቃዱ ለዚህ ለተገለጠለት እውነተኛ ጌታ ሰጠና ባርያው ሆነለት። በዚህም በሮሜ መልእክቱ ጳውሎስ የሚያስተጋባው ይህንኑ ነው። ቀድሞ ሲገዛው የነበረውን ነገር ሁሉ እየካደ አሁን ስለተገዛለት ጌታ ይመሰክራል።

እኛም ዛሬ የሆንነው እንዲሁ ነው ። ቀድሞ ለምኞቶቻችንና ለአለም የተገዛን የኃጢአት ባርያዎች ነበርን።

> "እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፤ የማንታዘዝ፥ የምንስት፥ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባርያዎች የምንገዛ፥ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፥ የምንጣላ፥ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን።" (ቲቶ 3፥3)



# ክፍል ሁለት

## ለወንጌል የተለየ

> "... ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ።" (ሮሜ 1፥1-2)

መለየት የሚለው ቃል ቀድሞ ከነበሩበት ቦታ ወይም ሁኔታ ውስጥ ወጥቶ ወደ ተለየ ቦታ ወይም ሁኔታ ውስጥ መግባትን የሚያመለክት ቃል ነው። ስለዚህ ጳውሎስ ተለየሁ ሲል ከስም ለውጥ ጀምሮ፥ ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታና ስፍራ በመውጣት እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ሁኔታና ስፍራ መግባቱን ለመግለጽ ፈልጎ ነው።

የእግዚአብሔር ጥሪ አኗኗርንና አድራሻን የሚቀይር ጥሪ ነው። ዛሬ በእግዚአብሔር የተጠራን (ክርስቲያኖች ሁሉ) ሁኔታችንና አድራሻችን እንደ ቀድሞው እንዳይሆን ተለይተን ወጥተናል። እግዚአብሔር አብርሃምን " ... ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ ... ውጣ።" እንዳለው እኛንም በክርስቶስ በኩል ተለይተን እንድንወጣ አዞናል። ስለዚህ አዲስና ዘላለማዊ አላማ ይዘን፥ በኑሯችን፣ በውሏችንና በተግባራችን ከቀድሞ የተለየ ሕይወት ውስጥ ገብተናል። (ቆላስያስ 1፥13)

1. በዚህ ይስማማሉ? ለምን? ከተስማሙ አሳቡን በራስዎ አባባል ሰፋ አርገው ይግለጹ? ካልተስማሙ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ተመስርተው ያልተስማሙበትን ምክንያት ያስረዱ።

በዚህ በቁጥር አምስት ላይ ሁለት ዋና ዋና ቃሎች ተጠቅሰዋል። እነዚህ ቃሎች፥ "ለእግዚአብሔር" የሚለው ቃልና "ወንጌል" የሚለው ቃል ናቸው።

2. ይህ ለእግዚአብሔር የሚለው ቃል ከሐዋርያው ጳውሎስ መለየት ጋር በተያያዘ ምንን ይገልጻል?

በዚህ ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የተለየን ወገኖች፥ የተለየንበት ምክንያት ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንድንሆነውና ፈቃዱ በኛ እንዲከናወን ነው። የእስራኤል ሕዝብ በፈርዖን አገዛዝ ስር ከነበረችው ከግብጽ ባርነት ነጻ ሲወጣ፥ የነፃነታቸው ዋና ምክንያት ልዑል እግዚአብሔርን ያመልኩና ያገለግሉ ዘንድ ነው። ወገኖች፤ ተለይተን መጠራታችን ለእግዚአብሔር መሆኑን አበክረን ማሰብና ለልባችን በየዕለቱ መናገር አለብን። ያን ጊዜ እግዚአብሔር የሚፈልገውን መፈለግ ልንጀምር እንችላለን።

3. ወንጌል የሚለው ቃልስ ስለ ጳውሎስ መለየት ምን የሚገልጸው ነገር አለ?

4. በሉቃስ 4፥17-19 መሰረት ይህ የምስራች ወይም ወንጌል ምን ይመስልዎታል?

ወንጌል ለአለም ሕዝብ ሁሉ የሚሆን መልካም የነጻነት ዜና ቢሆንም እንኳን፥ በአዲስ ኪዳን ላይ ድንገት ብቅ ያለ አዲስ ነገር አይደለም። ይልቁንም፥ "... በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ..." የተሰጠ፣ ለአባቶችም አስቀድሞ የተሰጠ ነበር። (ሮሜ 1፥2፣ የሐዋርያት ሥራ 13፥32)

ይህ ጌታ እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠው ተስፋ በአዲስ ኪዳን ዘመን በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጸመ። ይህ በክርስቶስ ተፈጽሞ ዛሬ ለአለም ሕዝብ ሁሉ የሚታወጀው የምስራች፥ የሰውን ሕይወት ወደመልካም የሚቀይር መልካም ዜና ከመሆኑም ባሻገር የእግዚአብሔርን ታማኝነት ይመሰክርልናል። ስለዚህ እርሱ በሚሰጠን ተስፋ በሙሉ ልብ ታምነን ልንጠብቀው እንችላለን። ጌታ እግዚአብሔር ቃሉን ለዘላለም ይጠብቃልና።

> " አምላክህ እግዚአብሔር መሃሪ አምላክ ነውና አይተውህም፥ አያጠፋህምም፥ ለአባቶችህም የማለላቸውን ቃል ኪዳኑን አይረሳም።" (ዘዳግም 4፥31)

ወገኖች፤ እግዚአብሔር ዛሬ ለሕይወታችን ምን ተስፋ ሰጥቶናል? እግዚአብሔር ለሰጠን ተስፋ ምን አይነት ምላሽ እየሰጠን ነው? ምን አልባት ሁኔታዎች ተስፋ አስቆርጠውን



ጥበቃችንን ትተን ይሆን? ምናልባት እግዚአብሔር የረሳን ወይም የተናገረንን ችላ ያለው መስሎን እኛም የተሰጠንን ተስፋ ትተነው ይሆን? ወይስ እኛ በራሳችን ጉዳይ ተይዘን የተሰጠንን ቃል ኪዳን ስለረሳን ጌታ እግዚአብሔርም ቃል ኪዳኑን የረሳ መስሎን ይሆን?

ጌታ መቼም ቢሆን ቃል ኪዳኑን አይረሳም። "ነገር ግን በሕፃንነትሽ ወራት ከአንቺ ጋር ያደረግሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ የዘላለምንም ቃል ኪዳን አጸናልሻለሁ።" (ሕዝቅኤል 10፥60) ብሎ እስራኤልን ያሰበ አምላክ ዛሬም ለኛ የሰጠውን ቃል ኪዳን ስለ ታመነው ስሙ ብሎ ይጠብቃል፤ የዘላለምንም ቃልኪዳን ያጸናልናል!

ዛሬ ሁላችን ከእግዚአብሔር ከተቀበልነው ተስፋ የተነሳ የምንጠባበቀው ነገር አለን። እርሱም ጌታ ኢየሱስ ዳግም ተገልጦ ከዚህ የመጠበቅ ኑሮ ወጥተን ወደ ዋናውና ዘላለማዊ ኑሮአችን የምንገባበትን ቀን ነው። ይህ ደግሞ እንደተባለው ይፈጸማል!

> "መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ። ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ። እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።" ማቴዎስ (24፥31-35)

ወገኖች፤ የዛሬ ኑሮአችን፥ ባለጉዳዮች የጉዳዩ አስፈጻሚው ወይም ፈጻሚው ቢሮ እስኪገቡ ድረስ ቁጭ ብለው የሚጠባበቁበት መጠበቂያ ክፍል እንደ ተቀመጡ አይነት ነው። በዚያ መጠበቂያ ሥፍራ፥ በቲቪ የሚታዩ ትእይንቶች፣ በጠረጴዛና በመደርደሪያ ላይ የሚቀመጡ መጽሔቶች፣ ለማረፊያ የተዘጋጁት መቀመጫዎች፣ በክፍሉ ዙሪያ የሚቀመጡት አበቦች፣ ጌጣጌጦችና የመሳሰሉት፥ በቆይታው ወቅት ሰው ሳይሰለች እንዲጠብቅ ለማድረግ እንጂ ረክቶበት እንዲመለስ የተዘጋጁ፥ የመጣበት ዋና ጉዳዮች አይደሉም።

የመጡበትና የሚጠብቁት ዋና ጉዳይ ያለው ጉዳይ አስፈጻሚው ወይም ፈጻሚው ዘንድ ስለሆነ ዋናውን ጉዳይ በመናፈቅ በትዕግስት ቁጭ ብሎ መጠበቅ የግድ ነው። ወገኖች፣ እኛ በክርስቶስ ድነን የጌታን ዳግም መምጣት የምንጠባበቅ ሁላችን፥ በዚህ አለም እንደ ባለጉዳይ ሆነን ነው የምንኖረው። ጉዳያችን ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ነው። እርሱ እስኪመጣና ፊቱ እስክንቀርብ ድረስ እኛም በዚህ አለም በተመደበልን ቦታ ሆነን እንጠባበቃለን። ስንጠብቀው ግን ልባችን እርሱን እርሱን እያለ፣ አይኖቻችን መገለጡን እየናፈቁ፣ አካላችን ጸድቶና ተዘጋጅቶ ነው። ጌታ ኢየሱስ ድንገት ይመጣል!

ጳውሎስ ሕይወቱ ወንጌል በመሆኑ ወሬውና ጥበቃው ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ በዚህ ክፍል (ሮሜ 1፥2-3) ላይ ይገልጻል። በዚሁ ምዕራፍ ላይ በቁጥር ሁለትና ሦስት ላይ ደግሞ ጳውሎስ በቁጥር 16 ላይ ደግሞ ስለጠቀሰው ስለወንጌል አጠቃላይና አጠር ያለ ትንታኔ

ከሰጠ በኋላ፥ በቁጥር አምስት ላይ ስለራሱ መናገር ይቀጥላል።

5. በዚህ ክፍል ጳውሎስ ወንጌልን የገለጸው እንዴት ነው?

ወንጌል “ … በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ … “ የሚለው ቃል የወንጌል ታሪክ አመጣጥና ምንነት ይገልጻል።

6. ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር የተወለደ መሆኑን የሚገልጸው ቃል የወንጌል መካከለኛ ስለሆነው ጌታ ኢየሱስ ምን ይገልጻል?

7. “… እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ …” የሚለው ቃል ስለ ጌታ ኢየሱስ ምን ይገልጣል?

ጌታ ኢየሱስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ ሆኖ አለምን ሁሉ ሊታዳግ የተገለጠ አዳኝ ነው። (ዮሐንስ 1፥14)

በሮሜ 1፥5 ላይ ተገለጠ የሚለው ቃል የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ በግብታዊነት የሆነ ነገር ሳይሆን አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፈቃድ ተወስኖ በመዘጋጀት ለኛ የተገለጠ መሆኑን ይገልጻል።

<u>በእምነት የሆነ መታዘዝን ለማፍራት ያቀደ (1፥5)</u>

*“በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤”*

8. በቁጥር አምስት ላይ ስለራሱ የሚናገርውስ ምንድን ነው?



ጸጋ በተቀባዩ ማንነት ላይ ያልተመሠረተና እግዚአብሔር እንዲሁ በነጻ የሚሰጠው ነገር ነው። ስለዚህ ጳውሎስ በተማረው ትምሕርት ወይም በዘሩ ሳይሆን፥ እንዲሁ በነጻ የማይገባውን የሐዋርያነት ጸጋ ተቀበለ።

በዚህ በቁጥር አምስት ላይ ጳውሎስ ጸጋንና ሐዋርያነትን የተቀበለበትን ምክንያት ሲገልጽ “በእምነት የሆነ መታዘዝን … “ ለማፍራት እንደሆነ ነው የሚገልጸው።

9. ጳውሎስ ከእምነት የሆነ መታዘዝ ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልዎታል?

እውነተኛ እምነት መታዘዝን ያስከትላል። ሥራ ወይም ተግባር የሌለው እምነት እንዳለ አይቆጠርም። ስለዚህ ጳውሎስ የተጠራው ሰዎች የክርስቶስን የማዳን ዜና ሰምተው እንዲደነቁ ብቻ ሳይሆን በወንጌል አምነው፥ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ እየተገዙ ወይም እየታዘዙ እንዲኖሩ ለማድረግ ነው።
በዚህ ክፍል ጳውሎስ ከእምነት የሆነ መታዘዝ ሲል፣ ከእምነት ያልሆነ መታዘዝ እንዳለ ይጠቁማል። ከእምነት ካልሆነ መታዘዝ መካከል ደግሞ ምናልባት፥ ከፍርሃት የሆነ መታዘዝ፣ ለታይታ ወይም ለይምሰል መታዘዝ፣ ከጥቅም የተነሳ መታዘዝና የመሳሰሉት ሊገኙበት ይችላሉ።

ወገኖቼ፤ እኛስ ለጌታ እየተገዛን ወይም እየታዘዝን ነው የምንኖረው? የኛ መታዘዝ ከምን የሆነ ይሆን? በግልዎ ያስቡበት!!!

10. ከዛሬው ጥናት ምን ያስተዋሉት ነገር አለ?

## ክፍል ሦስት

### በሮም ያሉትን ወገኖች በተመለከተ (6-8)

> በእነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ። በእግዚአብሐር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ። (ሮሜ ፲፥6-8)

ጳውሎስ በሮም ለነበረቸው ቤተ ክርስቲያን ወገኖች በጻፈው የመልእክቱ ክፍል፥ *" ... በእነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ።"* በማለት ለክርስቶስ በመገዛት እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው ሕይወት የመግባት ጥሪ በሮም ላሉ አሕዛብ ለነበሩትም እንደ ደረሰ ያረጋግጣል።

ይህ ጥሪ፥

- ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ጥሪ ነው። ማለትም ከተቀበሉት ውስጥ ማንም የተገባውና ብቁ ሆኖ ተገኝቶ አልነበረም።
- የከበረ ጥሪ ነው። ምክንያቱም ጠሪው ክቡር ጌታ እግዚአብሔር ስለሆነና የጥሪው አላማ ለማክበር ስለሆነ ነው። (ሮሜ 8፥30)

1. በቁጥር ሰባት ላይ ጳውሎስ ሮም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ስላሉ ወገኖች ምን ይላል?

________________________________________
________________________________________
________________________________________

ብዙ ጊዜ ሰዎች ራሳቸውን ከዘራቸው፣ ከቁመናቸው፣ ከትምሕርታቸው፣ ከሚሰሩት ሥራና ከመሳሰሉት አኳያ ይገልጹታል። ምናልባት ዛሬ እያንዳንዳችን፥ "ተነስታችሁ ራሳችሁን አስተዋውቁ።" ብንባል ወደ አዕምሮአችን ቶሎ የሚመጡልን ነገሮች መካከል፥ ስማችን፣ ውሎአችን፣ ሙያችንና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። ስለ እኛ አስተዋዋቂ የማይፈልገው እግዚአብሔርስ እኛን ማን ይለን ይሆን?

በዚህ ክፍል ጳውሎስ የሚገልጸው፥ እግዚአብሔር ሮም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ስላሉ ወገኖች የሚለውን ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፥ በሮም የሚገኙ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር የተወደዱ መሆናቸውን ያረጋግጥላቸዋል። ምን አልባት ከዚህ በፊት አሕዛብ መሆናቸውን፣ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ብቁ አለመሆናቸውንና የመሳሰሉትን ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ሰምተው ይሆናል። ሆኖም ግን ጳውሎስ እውነታው የተለየ መሆኑን ነው የሚገልጽላቸው።



ወገኔ፤ ሰው ስለርስዎ ምን ይላል? እርስዎስ ስለራስዎ ምን ይላሉ? ዛሬ ምን አልባት ራስዎን ሲመለከቱት፣ በወላጆችዎ፣ በወዳጅና ጓደኞችዎ የተባሉትን ሲያስታውሱና የተባሉት አሉታዊ ነገሮች በጆርዎ ሲስተጋቡ፥ በእግዚአብሔር ፊት ቀና ብለው እንዳይሄዱ አጉብጦዎት ይሆናል።

ወገኔ፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደገለጸው፥ ምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ይሁኑ፣ ምንም አይነት ተግባር ያድርጉ፣ እርስዎ በጌታ የተወደዱ ነዎት። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ጉያ ቀርበው ከእርሱ ጋር እንዳይጓዙ ድፍረት ያሳጣዎትን አስተሳሰብ ሁሉ አራግፈው መወደዱን እንደሚያውቅ ልጅ ወደ አባትዎ ጉያ ዘልቀው ይግቡ፤ የተሸከሟቸው የማይረቡ ነገሮች ቢኖሩ እንኳን እርሱ ሸክምዎን አራግፎ ያሳርፍዎታል። ጌታ በጣም ይወድዎታል!

2. እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ እንደሚወድ በዮሐንስ 3፥16 ላይ ገልጿል። ታድያ እነዚህ የአለም ሕዝቦች በሙሉ በሮም ቤተ ክርስቲያን እንደ ነበሩት ወገኖች በእግዚአብሔር የተወደዱ ሊባሉ ይችላሉ?

________________________________________
________________________________________
________________________________________

ይህ የእግዚአብሔር መውደድ አጋፔ ወይም ምክንያት የለሽ ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ሁኔታዎችም ሆኑ ሰው የሚያደርጋቸው ነገሮች ፍቅሩን ሊቀንሱና ሊጨምሩ አይችሉም። ስለዚህ በእግዚአብሔር ለመወደድ መስፈረት ስለሌለው መስፈርቱን የማያሟላ ማንም ሰው የለም። እግዚአብሔር - ሁሉን በታላቅ ፍቅር ይወዳል። ለዚህም ማረጋገጫው ደግሞ አንድያ ልጁ ስለሁሉ ሰው መስዋዕት ሆኖ እንዲቀርብ መስጠቱ ነው።

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ፍቅር አጥር እንዳለው ተደርጎ የሚታሰብበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ማለትም፥ የእግዚአብሔር ፍቅር፥ በክርስቶስ ላሉት ብቻ የሆነ ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል። ነገር ግን በዮሐንስ 3፥16 ላይ እንደ ተገለጸው እግዚአብሔር አለሙን ሁሉ የወደደው ጌታችን ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ዋጋ በመክፈል ሰውን ሁሉ ንጹሕ ካደረገ በኋላ አይደለም። ይልቁንም እግዚአብሔር አለሙን ሁሉ አስቀድሞ ስለወደደ ነው ክርስቶስን የላከው። ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር ሁሉንም በእኩል ይወዳል። የእግዚአብሔር ፍቅር ሁሉን የሚያጠቃልል እንጂ የሚለያይ አይደለም።

እግዚአብሔር ያልዳኑትን ባይወድ ኖሮ እኛ ዛሬ ስንመሰክር ጳውሎስ በሮም የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ላሉ ወገኖች እንዳለው "እግዚአብሔር ይወዳችኋል!" ማለት ባልተገባን ነበር። ነገር ግን በርግጥ እግዚአብሔር ሁሉንም በፍጹም ፍቅር ስለሚወድ እየተወደዱ ከርሱ ለራቁት እንራራለን፤ እኛ ደግሞ ይህን ፍቅር እንድንረዳ ስላረገንና በፍቅሩ ጥላ ስር እንድንገባ ስለረዳን በምሥጋና ጌታን እናከብረዋለን።
እግዚአብሔር ሁሉን ይወዳል ስንል ደግሞ አንድ የሃገር መሪ ተነስቶ የሃገሬን ሕዝብ

እወዳለሁ እንደሚለው የጅምላ መውደድ አይደለም። ይልቁንም አውጉስቲን የተሰኙ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ሰው እንደ ተናገሩት፥ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ከእርሱ ሌላ የሚወደድ ማንም እንደሌለ አደርጎ ነው የሚወደው። (God loves each one of us as if there was only one of us to love.)

3. ታድያ እግዚአብሔር ሁሉን በእኩል ከወደደ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወይም አረማመዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ሰው ምን የተለየ ቦታ አለው? ለምን?

________________________________________________

________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

የእግዚአብሔር ሞገስ (God's favor) ለአንድ ሕዝብ፣ ሕብረተሰብ ወይም ግለሰብ ከሌላው ይልቅ በተለይ ሊበዛ ይችላል። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰፈሩ የተለያዩ ታሪኮች ላይ ጎልቶ የሚታይ ነው። ከነዚህ ውስጥ የሞት መልአክ በግብጻውያን ድንኳን የሚገኙትን የበኩር ልጆች ሲገድል በእስራኤላውያኖች ድንኳን ግን የተለየ ጥበቃ ከመደረጉ የተነሳ የሞት መልአክ እንዳለፋቸው የሚናገረው ታሪክ አንዱ ነው።

ታድያ እግዚአብሔር ሁሉን የሚወድ ከሆነ ለምን እንዲህ ይለያል?

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሊሆኑ ከሚችሉ ሃሳቦች መካከል "ሰው ባለው የመምረጥ ነጻነት ተጠቅሞ በሚወስደው እርምጃ ልዩነት ሊፈጥር ይችላል።" የሚለው አንዱ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወይም በምክንያት የለሽ ፍቅር (unconditionally) ቢወድም እንኳን፥ ለሁሉ ነጻ ያቀረበውን ፍቅሩንና የፍቅሩን ፍሬ ለመቀበል ቅድመ ሁኔታ (condition) አስቀምጧል። ይህ ቅድመ ሁኔታ ምርጫ ይባላል። ስለዚህ ልዩነት የሚፈጥረው ነጻነትን መሰረት ያደረገው የሰዎች ምርጫ ነው።

በነገራችን ላይ ይህ ቅድመ ሁኔታ የሰዎችን ማንነት የሚመዝን ሳይሆን የሰውን ፈቃድ የሚያከብር ወይም የሚጠይቅ ነው። ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር ጨዋ አምላክ ስለሆነ የሰውን ፈቃድ አይነካም። ከአዳምና ከሄዋን ጀምሮ ያሳየው ይህንኑ ባሕሪውን ነው። እግዚአብሔር ምርጫ ይሰጣል እንጂ አስገድዶ ፍቅሩንና ቸርነቱን አይግትም። ስለዚህ በመጀመርያ ደረጃ ሰዎች በፈቃዳቸው እግዚአብሔር ወደ ከፈተው ሰማያዊው ቤተሰብ በአባልነት ይገባሉ። ሌሎች ደግሞ በምርጫቸው የተከፈተውን በር ይተዉታል። ስለዚህ፥ እግዚአብሔር እሺ ያለውንም እምቢ ያለውንም ሰው በእኩል ቢወድም እንኳን የቤተሰቡ ተካፋይ የሚሆኑት ግን በፈቃዳቸው ወደዚህ የፍቅር ጥላ የገቡት ብቻ ናቸው።



ሮም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ለነበሩ ክርስቲያኖች በተጻፈው የጳውሎስ መልእክት፥ ሰዎች ለአለም ሁሉ የቀረበውን የእግዚአብሔርን ምክንያት የለሽ ፍቅር በመቀበል ጌታ ይወዳችኋል ከመባል አልፈው በጌታ የተወደዳችሁ ወደ መባል መሸጋገር እንደሚያስፈልግ ያሳያል። "ጌታ ይወዳችኋል!" ለሁሉም ይሰራል ነገር ግን በእሺታ ፍቅሩ በሕይወታችን ተግባራዊ ሆኖ እንዲሰራ (activate) ሲደረግ "በጌታ የተወደዳችሁ!" የምንባል እንሆናለን።

ስለዚህ ጳውሎስ ሮም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ክርስቲያኖች ጌታን በመቀበል የእግዚአብሔር ፍቅር በእነርሱ እንዲሰራ ስለ ፈቀዱ፥ በእግዚአብሔር የተወደዱ የመባል ቅድሚያ እንዳገኙ ያረጋግጥላቸዋል።

4. ጳውሎስ በሮም ቤተ ክርስቲያን የነበሩትን ክርስቲያኖች የሚገልጽበት ሌላው ቃል ምንድን ነው? ይህ እነርሱን ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል ትርጉም ወይም ትንታኔ ምንድን ነው? (ሮሜ 1፥7)

________________________________________________

________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ቅዱስ መሆን የክርስቶስ ከመሆን የሚመነጭ ነው ወይም የክርስቶስ የመሆን ውጤትና ትሩፋት ነው (የሐዋርያት ሥራ 26፥18)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባከናወነው ሥራ ወደ ሕይወታችን መዝገብ (አካውንት) የእርሱ ቅድስና ስለተጨመረልን፥

1. የኃጢአት ዕዳችን ሙሉ ለሙሉ ተሰረዘ
2. የሕይወታቸን አካውንት በክርስቶስ ቅድስና ተሞልቶ ቅዱሳን ተደረግን።

5. ይህ ባለ ሁለት ነጥብ ሃሳብ ገብቶዎታል? እስቲ የተረዱትን በራስዎ አባባል ይግለጹት? አሳቡ ካልገባዎት መሪውን በመጠየቅ ይነጋገሩበት።

________________________________________________

________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በቁጥር ሰባት ላይ የተጠቀሰው፥ *" … ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።"* የሚለው የጳውሎስ ሰላምታ ሁለት የተለያዩ ማኅበረሰቦችን የሰላምታ አሰጣጥ ዘይቤዎች ያቀፈ ነው።

"ጸጋ" (charis) የሚለው ቃል፥ በግሪክ ማኅበረሰብ ዘንድ የተለመደ የሰላምታ አሰጣጥ ዘይቤ ሲሆን፥ "ሰላም" (shalom) የሚለው ቃል ደግሞ በአይሁድ ማኅበረሰብ ዘንድ የተለመደ የሰላምታ አሰጣጥ ዘይቤ ነው።

6. ለመሆኑ በጳውሎስ መልእክቶች መሰረት የነዚህ ቃላት ትርጓሜ ምን ይመስልዎታል? የቃላቱ አቀማመጥ በሰላምታው ላይ በሰፈረው ቅደም ተከተል መሰረት መሆኑ ምክንያት ያለው ይመስልዎታል? ጳውሎስ ጸጋን አስቀድሞ ሰላምን ያስከተለው ሆነ ብሎ ነው ወይስ የልማድ ወይም ያጋጣሚ ጉዳይ ነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

በዚህ በቁጥር ሰባት ላይ ጳውሎስ ጸጋንና ሰላምን የሚሰጡን እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር ወልድ እንደ ሆኑ አርጎ ቢያስቀምጥም እንኳን፥ ይህ አካል አንድ መሆኑን ለመግለጽ፥ "... ከእግዚአብሔር ከአባታችን እና ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን ..." ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ..." በማለት ነው ሰላምታውን ያሰፈረው።

7. በሮሜ 1፥8 መሰረት ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው ለምንድን ነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

በዚህ ጥናት መግቢያ ላይ እንደተገለጸው፥ መልእክቱን ተቀብለው ለሚያስተላለፉት ቀዳሚ አንባቢዎቹ ሰላምታን መስጠትና ማስገንዘብ የፈለገው ነገር ስለነበረ፥ "አስቀድሜ" የሚለውን ቃል በመጠቀም ወደ መልእክቱ ዝርዝር ከመግባቱ በፊት በሮም ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ክርስቲያኖች እንዲገነዘቡት የፈለገውን ነገር ይገልጻል። ስለዚህ ይህ "አስቀድሜ" የሚለው ቃል፥ ጳውሎስ የሚገልጸው ነገር ከሌሎች ተከታይ አሳቦቹ የላቀ መሆኑን ለመግለጽ ሳይሆን መጀመሪያ በሮም ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ክርስቲያኖች ጌታን ስለ እነርሱ እንደሚያመሰግን ለመግለጽ ነው።

በዚህ የጳውሎስ ሰላምታ ላይ ልናተኩርበት የሚገባን አንድ ነገር ቢኖር፥ ምሥጋናውን ያቀረበው በሮም ቤተ ክርስቲያን ለሚገኙ ክርስቲያኖች ሳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለአምላኩ ነው።

8. ለምን ይመስልዎታል? ምሥጋናውን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያቀርበው ለምን ይመስልዎታል?



________________________________________

________________________________________

በሮም ቤተ ክርስቲያን ያለው እምነት በዓለም ሁሉ መሰማቱ፥ " በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።" ተብሎ የነተነገረው፥ ቅደም ተከተሉን ይዞ በመፈጸም ላይ እንዳለ ያሳያል። ስለዚህ ጳውሎስ ጌታን እጅግ አድርጎ ያመሰግናል።

9. ዛሬ እርስዎ እግዚአብሔርን በብዛት የሚያመሰግኑት ስለምንድን ይሆን? ከዛሬው ጥናት ምን አስተዋሉ?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

# ክፍል አራት

## በሮም ያሉትን ወገኖች በተመለከተ (9-15)

በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና፤ ምናልባት ብዙ ቆይቼ ወደ እናንተ አሁን እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ እየለመንሁ ሁልጊዜ ስጸልይ ስለ እናንተ ሳላቋርጥ አሳስባለሁ። ትፀኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና፤ ይህንም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው። ወንድሞች ሆይ፥ በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ እንደ ሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም፥ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ፤ ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ። (ሮሜ 1፥9-15)

**በሮሜ 1፥9-10 ላይ ባለው ክፍል፥ ጳውሎስ በሮም ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ወገኖችን ለመጎብኘት ያለውን ጥልቅ ፍላጎት ይገልጻል።**

1. **በዚህ ክፍል ላይ፥ “ በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገልግለው እግዚአብሔር ...” ሲል ምን ማለቱ ነው?**

________________________________________

________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

2. **በቁጥር ዘጠኝ ላይ፥ ጳውሎስ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው የሚለው ምንን በተመለከተ ነው? መሃላ ነው? መሃላ ይፈቀዳል እንዴ?**

________________________________________

________________________________________

**በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ ጸሎት ከፍተኛ ስፍራ እንዳለው የጳውሎስ መልእክቶች ይመሰክራሉ። “ሳታቋርጡ ጸልዩ ... ” በማለት ከመምከር ባሻገር ራሱ ሳያቋርጥ ይጸልይ እንደነበረ በሮሜ መልእክቱ ላይም ተገልጿል።**

**በዚህ ክፍል ጳውሎስ፥ “ሁልጊዜ” እና “ሳላቋርጥ” በሚሉ ቃላቶች ነበር - በምን አይነት መልኩ ይጸልይ እንደ ነበረ የሚገልጸው። ምንም እንኳን በሚጸልይበት ጉዳይ ላይ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ቢገጥመውም፣ ሩጫ ስለሚበዛበት ጊዜ ባይኖረውም ወይም ሊደክመው ቢችልም መጸለዩን ግን አላቋረጠም ነበር።**



**ወገኖች፥ ዘማሪ አዜብ ሃይሉ በጥሩ ዜማ እንደገለጸችው፥ ጸሎታችን በምንም ምክንያት መቋረጥ የለበትም። ሁልጊዜ ሳናቋርጥ፥**

**የሰማይ ዳርቻ ሰሪ**
**የምድር ሁሉ ፈጣሪ**
**አንተ አይደለህም ወይ እግዚአብሔር ኤልሻዳይ**
**ኧረ አንተ አይደለህም ሆይ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ**

**አላቋርጥም ማንኳኳቴን እስኪከፈትልኝ ደጁ**
**ጸሎቴንም (እስኪመልስ) እስኪዘረጋልኝ እጁ**
**ዘንብል እስኪል ከዙፋኑ እስኪበዛልኝ ምሕረቱ**
**ዝም አልልም አላቆምም መፈለጌን ማየት ፊቱን**

**እያልን ስለ ሃገሮች፣ ስለወገኖች፣ ስለቤተሰቦች፣ ስለራስና ስለ ተለያዩ ጉዳዮች በጸሎት መትጋት ያስፈልጋል።**

**የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር፥ “ ... የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።” ይላል።**

**ደቀ መዛሙርት የጸሎትን አስፈላጊነት ከጌታ ከኢየሱስ ሕይወትና ትምሕርት ተገንዝበዋል። ክርስቶስ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዴት እንደሚጸልዩ አስተምሯቸውም ነበር። ስለዚህ እኛም በነገር ሁሉ ሳናቋርጥ ልንጸልይ ያስፈልጋል።**

**በጳውሎስ ጸሎት ውስጥ ሌላው ሳንገነዘብ ማለፍ የሌለብን ነገር ቢኖር፥ የፍላጎቱን መከናወን ለእግዚአብሔር ፈቃድ መተዉን ነው። ጳውሎስ ስለፍላጎቱ አለማቋረጥ ቢጸልይም የግድ የኔ ይሁን በሚል ስሜት ሳይሆን፥** “ ... በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዴን እንዲያቀናልኝ ... ” **በሚል ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይገዛ እንደነበር እናያለን።**

**ወገኖች፤ እግዚአብሔር ጸሎታችንን በተለያየ መንገድ ሊመልስ ስለሚችል መልሱንና አሰራሩን ለእርሱ መተዉ መልካም ነው። ምናልባት አንዳንዴ መልሱ እኛ እንደጠበቅነው ላይመጣ ይችላል። ጳውሎስ ሲጸልይ እስረኛ ሆኖ ወደ ሮም እንደሚሄድ አላወቀም ነበር። ነገር ግን መልሱ የመጣው በዚያ መልኩ ሆነ። ይሄም ደግሞ ለመልካም ነበር። እንዴት?**

**አንድ አድሜያቸው የገፋ ክርስቲያን ሴት ጠዋት ጠዋት እየተነሱ በከፍተኛ ድምጽ “ጌታ ይመስገን!” በማለት የክርስቶስን ጌትነት ያውጁ ነበር። ታዲያ የነኚህ ሴት ጎረቤት የነበሩ በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ አዛውንት፥ በነገሩ እየተበሳጩ፥ “ እባክዎት ዝም ብለው አይድከሙ፥ ጌታ ኢየሱስ የሚባል የለም!” በማለት ያላግጡባቸው ነበር።**

**አንድ ቀን እኚህ ክርስቲያን አዛውንት እንደ ወትሮዋቸው ጠዋት ተነስተው ከፍ ባለ ድምጽ፥ “ምንም እንኳን በቤቴ የሚላስ የሚቀመስ ባይኖረኝም፥ ኢየሱስ ጌታ ነው!” ብለው በታላቅ**

ድምጽ ተናገሩ። ታዲያ ይህን የሰሙት በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑት አዛውንት፥ ገበያ ሄደው የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችን በመግዛት የክርስትያንዋ አዛውንት ቤት ደጃፍ ላይ አስቀምጠው ሄዱ።

በነጋታው እኚህ ሴት በጠዋት ተነስተው እንደለመዱት ከፍ ባለ ድምጽ፥ " የሚያስፈልገኝን ጠይቄ በበሬ ላይ ያስቀመጠልኝ ኢየሱስ ጌታ ነው!" ባሉ ጊዜ በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑት አዛውንት፥ "አይ ሞኝ … ይህን ምግብ በደጅዎት ያስቀመጠው ጌታ ሳይሆን እኔው ነኝ … ጠዋት ጠዋት እየተነሱ ሲጮኹ የሚያደነቁሩት እኔን እንጂ ሌላ የሚሰማዎት የለም፤ እንዲያው ዝም ብለው ኢየሱስ ጌታ ነው አይበሉ።" አሏቸው። ያን ጊዜ ክርስቲያን አዛውንቷ፥ ድምጻቸውን ይባስ ከፍ አድርገው ፥ "የሚያስፈልገኝን ነገር ሰይጣን ከፍሎበት በደጄ እንዲቀመጥ ያረገልኝ ኢየሱስ ጌታ ነው!! አሉ ይባላል። (ሰውን ሰይጣን ማለት ግን ተገቢ ላይሆን ይችላል።)

ወገኖች፥ የጳውሎስ የጸሎት መልስም በተመሳሳይ በእስረኝነት ስም በሮም መንግስት ወጪ በሚደረግ ጉዞ የተዘጋጀ ነበር ። ጳውሎስ ወደ ሮም የሄደው በተለያዩ ከተማዎች ያሉ ክርስቲያኖች ባሰባሰቡለት ገንዘብ ወይም ድንኳን ሸጦ ባጠራቀመው ገንዘብ ሳይሆን የሮም መንግስት ከፍሎለት በነጻ ነው። ሮም እስረኛ የሆነው ደግሞ በተከራየ ቤት ውስጥ እንጂ ወህኒ ውስጥ አልነበረም፥ ሰለዚህ በሮም ቤተ ክርስቲያን ያሉ ወገኖችን ማግኘት ይችል ነበር። በእርግጥ ኢየሱስ ጌታ ነው!

ጸሎት ጌታን ማመን ነው ልንል እንችላለን። ምክንያቱም እምነት የሌለበት ጸሎት - ጸሎት አይደለም። እምነት ማለት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ሰጥቶ በመተው በእርግጠኝነት ምላሽ መጠበቅ ማለት ነው። ስለዚህ ሳናቋርጥ ስንጸልይ፥ የታመነው ጌታ እንደ ፈቀደው እንዲሰራ ፈቃዳችንን ለፈቃዱ ሙሉ ለሙሉ በማስገዛት እንዲሆን ያስፈልጋል።

3. ወደ ሮሜ ሰዎች መልእክት ምዕራፍ አንድ ቁጥር ዘጠኝና አስር ላይ የተገለጸው የጳውሎስ ጸሎት ማንንና ምንን የተመለከተ ነበር?

በአለም ዙሪያ በሮም ስለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን እምነት ይወራ እንደነበር በቁጥር ስምንት ላይ ተጠቆሟል። ቀደም ሲል በጥናት አንድ ላይ እንደተጠቀሰው፥ በሮም የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችውና ያደገችው በጳውሎስ ቀጥተኛ ያገልግሎት ተሳትፎ አልነበረም። ስለዚህ በአለም ዙሪያ ስለ እምነታቸው የሚነገርላቸው፥ እርሱ የመሰረታቸው ወይም ባገልግሎቱ ሥር የሚጠቃለሉ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩ አማኞች ሳይሆኑ፥ ጳውሎስ ከዚህ በፊት በአካል ባልጎበኛትና ምናልባት ስሙ አብሮ በማይጠቀስባት ቤተ ክርስቲያን የነበሩ አማኞች ነበሩ። ዛሬ በየአብያተ ክርስቲያናት አልፎ አልፎ እንደሚታየው ከሆነ፥ ይሄ ጉዳይ ለጳውሎስ ምንም ስሜት ላይፈጥርለት (ላይሞቀው ወይም ላይቀዘቅዘው) ወይም ከቅናት የተነሳ ደስ ላያሰኘው ይችል ነበር ።



ነገር ግን፥ ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ በጣም ከመደሰቱ በተጨማሪ በዚያ ሥፍራ ባለው እንቅስቃሴ ተካፋይ ለመሆን ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ይገልጽ ነበር።

በክርስቶስ መሰረት ላይ የቆመች አለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን አንድ ናት። ስለዚህ በአንድ አካል ላይ እንዳሉ ብልቶች በመንፈስ ተሳስረን፣ አንዱ ሲከበር ሌላው እየተደሰተና እያመሰገነ፣ ሲቻል ደግሞ አብሮ ለመስራት እየተጋን የጌታን፥ የእግዚአብሔርን መንግስት ማስፋፋት ይገባናል።

4. በሮሜ 1፥11-13 መሰረት ጳውሎስ በሮም ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ወገኖችን ለማየት የፈለገው ለምን ይመስልዎታል?

በጸሎቱ የተገለጸው የጳውሎስ ፍላጎት፥ ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ሰዎችና ለወገኖች ምን ያህል ፍቅርና የተሰጠ ልብ እንዳለው ያሳያል። ጳውሎስ የእረኝነት ልብ ስላለው ለበጎቹ የሚያነባና ሳያቋርጥ የሚጸልይ ታማኝ አገልጋይ ነበር። ምንም እንኳን ጳውሎስ በሮም ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ወገኖችን ከዚህ በፊት አይቶአቸው ባያውቅም፥ እጅግ ይወዳቸውና ሊያያቸው ይናፍቅ ነበር።

ወገኖች ፤ ይህ የክርስቶስ ወንጌል እንኳን በቅርብ ያሉ ወገኖችን ቀርቶ በሩቅ ያሉ ያልተያዩ ወገኖችን የሚያስተሳስር ኃይል አለው። ይህ ወንጌል ዛሬም በወገኖች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል። የወንጌሉ ኃይል ዛሬም ትኩስ ነው።

ስለዚህ በክርስቶስ የዳንን ሁላችን በፍቅር ተያይዘን የተሰጠንን ሃላፊነት በጋራ ለመወጣት መጣር አለብን። እርስ በርስ ከመቀናናት፣ ከመፎካከር (ለመበላለጥ) የጥላቻ ድንጋይ ከመወራወርና አንዱ ሌላውን ለማፍረስ ከመጣር ይልቅ፥ በመከባበር፣ በመደጋገፍና እርስ በርስ በመበረታታት፥ የተጠራንበትን አንድ አላማ በአንድነት መወጣት ይገባናል!

በቁጥር አስራ ሁለት እንደ ተጠቀሰው፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ሮም በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ወገኖችን ለመጎብኘት የሚሻበት አንዱ ምክንያት በተቀበሉት ወንጌል የሚጸኑበትን መንፈሳዊ ስጦታ ለማካፈል ነበር።

5. ይህ ጳውሎስ "መንፈሳዊ ስጦታ" የሚለው ምንድን ነው? እንዴት ነው ሊያካፍላቸው የሚችለው?

በዚህ የጳውሎስ መልእክት የመጀመሪያው ክፍል ከሌሎች መልእክቶቹ በተለየ ጳውሎስ “እኔ” የሚል ቃል በብዛት ቢጠቀምም እንኳን የራሱን ስም ከማዋደድ ወይም በራስ ከመኩራራት የመነጨ አይደለም። ምክንያቱም ከመጀመሪያ ጀምሮ ጳውሎስ ራሱን ባርያ እንደሆነ ቆ ነበር። ስለሆነው መልካም ነገር ጌታን እንጂ ራሱን አያወድስም ነበር። ሳያቋርጥ እንደሚጸልይ በመግለጽ በራሱ አንዳች ማድረግ የማይችል መሆኑን አስታውቆ ነበር። በተጨማሪም፣ “ … በእኔም እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው።” በማለት ራሱን ከሚያገለግላቸው ጋር ዝቅ አርጎ ገልጾ ነበር።

6. በቁጥር 13፥ “ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። በማለት ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄዱ በፊት የነበረውን እቅድ ያሳስባቸዋል። ለመሆኑ በእርስዎ ግምት ጳውሎስ በዚያን ጊዜ ወደ ሮም እንዳይሄድ የተከለከለው ለምን ይመስልዎታል?

ጳውሎስ ነጻ በነበረበት ጊዜ ሮም እንዳይሄድ ተክልክሎ ቢሆንም እንኳን ሮም ውስጥ እንደ ቁም እስረኛ በተከራየው ቤት ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ፣ በነጻነት ያስተምርና ወንጌልን ያዳርስ ነበር። የእግዚአብሔር አሰራር ይስደንቃል! ራሱ በወደደው መንገድ መስራት የሚችል አዋቂ አምላክ ነው!

7. ጳውሎስ ወደ ሮም ለመሄድ በተከለከለበት ጊዜ እንኳን ወንጌልን ሮም ለሚገኙ ሰዎች (ክርስቲያኖችንና ያላመኑትንም ሊያጠቃልል ይችላል።) ለማስተማር በምን አይነት ሁኔታ ላይ ነበር? (ቁ. 14፥15)

በቁጥር አስራ አራት ላይ፣ ጳውሎስ አደራውን ለመወጣት ሮም ለመሄድ እቅድ እንደነበረው



ይገልጻል። ይህ ጉዳይ በማቴዎስ ሃያ አምስት ላይ ስለ መክሊት የሚገልጸውን ታሪክ የሚያስታውስ ነው።

በማቴዎስ 25፥14-18 ላይ፣ “ ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ … ለእያንዳንዱ … ” መክሊት ሰጥቷቸው እንደ ነበር ይናገራል፣ ታዲያ ከነዚህ መካከል ሁለቱ እቅድ እንደ ነበረው ሰው ሄደው በተሰጣቸው መክሊት ሲያተርፉ፣ አንደኛው ግን ምን እንደሚያደርግ ግራ እንደገባው ሰው፣ መክሊቱን ቀብሮት ነበር።

ዛሬ እርስዎ እቅድ አለዎት? በተለይ ከእግዚአብሔር በተቀበሉት መክሊት ለማትረፍ ምን እቅድ አውጥተዋል? ያስቡበት!

8. ሌላው ደግሞ ጳውሎስ እቅድ አውጥቶ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን ታጥቆ በተጠንቀቅ እንደ ቆመ ወታደር ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል። ከዚህ ምን ይማራሉ? ከዛሬው ጥናትስ ምን ያስተዋሉት ወይም የቀረልዎት ነገር አለ?

# ክፍል አምስት

## ወንጌልን በተመለከተ (16-17)

> “በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።” (ሮሜ 1፥16-17)

በዚህ ክፍል ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን በተመለከተ ያለውን አቋም፣ የወንጌል፣ የወንጌልን አላማ፣ የወንጌልን አድማስና መሰረታዊ መልእክት ይገልጻል።

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ከግል ሕይወቱ ጋር በተያያዘ፥ ስለወንጌል ያለው አቋም ምን ይመስል ነበር? በቁጥር አስራ ስድስት መሰረት፥ እንዲህ ያለ አቋም ሊኖረው የቻለው ለምን ይመስልዎታል?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________________

____________________________________________________

____________________________________________________

በሮሜ 1፥16 ላይ ከተገለጸው ምክንያት በተጨማሪ በጊዜው ከነበረው ሁኔታ አኳያ የተለያዩ ምክንያቶችን መገመት ይቻላል። ለምሳሌ፥

ጳውሎስ በሚያገለግልበት ዘመን ሮማውያን አይሁዳውያንን በጣም ይንቁ ነበር፥ ይህ የወንጌል መካከለኛ ወይም ወንጌል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የይሁዳዊ አናጢ ልጅ እንደነበረ ይታወቃል። ስለዚህ፥ ታላላቅ ባለስልጣናት በሚኖሩባት፣ ጥበብና ስልጣኔ በተንሰራፋበት፣ አሕዛብ በሞሉባት ገናና ከተማ፥ ስለ አንድ በመስቀል ላይ እርቃኑን በውርደት ስለተሰቀለ አይሁዳዊ መናገር አሳፋሪ ሊመስል ይችላል።

ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥8 ላይ፥ “… በእስረኛው በእኔ አትፈር።” በማለት ጳውሎስ እስረኛ በመሆኑ እንዳይሸሸው ጢሞቴዎስን ያሳስበዋል፤ ምክንያቱም እስረኛ የመሆንን ያህል ዝቅ ካለ (በሰው ፊት ከተዋረደ) ሰው ጋር መተባበር አሳፋሪ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ እንደ ወንበዴ ተይዞ በሮም ልማድ መሰረት ትልቅ ውርደት በሆነው በመስቀል ሞት ከተቀጣው ከይሁዳዊው ከኢየሱስ ጋር መተባበር አሳፋሪ ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪም፥ አማኞች በሚንገላቱበትና በሚገደሉበት ከተማ ሊከተል ከሚችለው ውርደትና መከራ የተነሳ፥ ወንጌልን ለመስበክ ቀርቶ ክርስቲያን መሆንን ለመግለጥ እንኳን አስፈሪና



አሳፋሪ የሆንበት ጊዜ ሊኖር እንደሚችል ይገመታል።

ሆኖም ግን ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ የተረዳው እውነት ስላለ፥ “የፈለገ ቢሆን በወንጌል እኮራለሁ እንጂ አላፍርም።” የሚል ሃሳብ ያዘለውን አቋሙን ይገልጻል።

ጳውሎስ ኢየሱስን ሰዎች እንደሚሉት ሳይሆን የጌታን እውነተኛ ማንነት አውቋል። በደማስቆ መንገድ ላይ በሚያስደንቅ ብርሃን ተገልጦለት አምላክነቱን ተረድቷል። ስለዚህ ለጳውሎስ፥ ይህ ኢየሱስ ምስኪንና ተራ አይሁዳዊ ሳይሆን ራሱን ስለ እኛ ብሎ ራሱን ዝቅ በማድረግ ተገልጦ የነበረ፥ አሁን በአብ ቀኝ በታላቅ ክብር ውስጥ የሚኖር፥ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ የነበረ፣ ያለና ዘላለም የሚኖር አምላክ ነው።

ነገስታትን ጨምሮ በምድር ላይ የከበሩ ሰዎችና ነገሮች ሁሉ ክብራቸው ዛሬ ታይቶ ነገ እንደሚጠወልግ አበባ ነው። ሁሉም እየጠወለጉ በየተራ ያልፋሉ፣ ስለዚህ ምንም አያስመኩም። ሰው እርቃኑን እንደመጣ እርቃኑን በሚመለስ በሰው ሲታመን ያሳፍራል፣ ሰው ዛሬ ደምቆ ነገ በሚጠፋ ወይም በሚሰለች ነገር ሲኮራ ያሳፍራል። ዝናው በአለም ላይ የገነነው ኢየሱስ ግን የሚያኮራና የሚያስመካ ጌታ ነው!

> እርሱ እንደ ማለዳ ብርሃን፣ እንደ ጸሃይ አወጣጥ፣ በጠዋትም ያለ ደመና እንደሚደምቅ፣ ከዝናብም በኋላ በምድር እንደሚበቅል ልምላሜ፥ ዘላለም በክብሩ እያበራ የሚኖር ክቡር ንጉስ ነው።
>
> ግርማዊነቱ ወደር የለው፣ ዙፋኑ አቻ የለው፣ ሥልጣኑ መሳይ የለው፣ መንግስቱ እኩያ የለው፣ በሚያስፈራ ግርማ የደመቀ፣ በተንቆጠቆጠ ክብር የተጥለቀለቀ፣ የሰማይን አዕማድ በተግሳጹ የሚያንቀጠቅጥ፣ ባፉ ነበልባል ምድርን የሚያጠራ፣ ባፍንጫው እስትንፋስ ውኆችን የሚከምር።

አቤቱ ፥ በአማልክት መካከል እንደ ኢየሱስ ማን ነው?!

> ሞት የማይዘው፣ ተራሮች የማያቆሙት፣ ደመና የማይጋርደው፣ ጊዜ የማይገድበው ፣ መንግስቱን የሚወስን አድማስ የሌለው፣ ሁሉን የሚገዛ፣ ነገስታት የሚንበረከኩለት፣ አሕዛብ የሚሰግዱለት፣ መላእክት ዘወትር የሚያመልኩት፥ በአምባላይ ፈርስ ተቀምጦ፣ በታላቅ ሰራዊት ተከቦ፣ በመላእት ዜማ ታጅቦ በክብርና በሃይል የሚገለጥ፣ የክብር ንጉስ ነው።

ይሄ የክብር ንጉስ፥

> በጨለማ ላሉ ብርሃን ያወጣል፣ ለድሆች መልካም ዜና ያበስራል፣ የተጠቁትን ነጻ ያወጣል፣ የተማረኩትን ይፈታል፣ ልባቸው የተሰበረን ይጠግናል፣ ሃዘንተኞችን ያጽናናል፣ ተስፋ የቆረጡትን ያበረታል፣ የቆሰሉትን ይጠግናል፣ የታመሙትን

ይፈውሳል፣ የሞቱትን ያስነሳል፣ የቆሸሹትን ያነጻል፣ የተጣሉትን ያነሳል፣
የተረሱትን ያስታውሳል፣ የተዋረዱትን ያከብራል፣ የጠፉትን ያገኛል፣ የተራቡትን
ያበላል፣ የተጠሙትን ያጠጣል፣ ደካሞችን ያሳርፋል …።

ኧረ ኢየሱስ ልዩ ነው
ተወዳዳሪ የሌለው
ታላቅ አምላክ እርሱ ነው።

ስለዚህ በእርሱ መጠራት፣ ሥራውን ማውራት ትልቅ እድልና ክብር ነው። "እናንተ መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥ የክብርም ንጉሥ ይግባ።" (መዝሙር 24፥7፣9)

እንደ ዳዊት ክብራችንን እንጣልና እናክብረው፣ እንደ ሐዋርያት ሳናፍር ዝናውን እናውጅ። ኢየሱስ ጌታ ነው!!

በክርስቶስ ኢየሱስ ስምና በቃሉ የሚያፍር ጌታ ማን እንደሆነ አላወቀም ማለት ይቻላል። ጌታን የማያውቅ ደግሞ በጌታ ዘንድ ላይታወቅ ይችላል! አይመስልዎትም?

በዚህም በዘማዊና በኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል። (ማርቆስ 8፥38)

የወንጌል መልእክት በውስጡ ካቀፋቸው መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል ሦስቱ፦

- የሰው ልጅ በኃጢአት እዳ ውስጥ መሆኑ
- በሞተው፣ ሞትን ድል አርጎ በተነሳውና ወደ ሰማይ ባረገው በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከኃጢአት እዳ ነፃ የመውጫ መንገድ እግዚአብሔር ማዘጋጀቱንና
- ይህ የነጻነት መንገድ ለሁሉ በነጻ መቅረቡ ናቸው።

2. በቁጥር 16 መሰረት የወንጌል ባህሪ ምንድን ነው? ጳውሎስ የገለጸውን ሃሳብ በራስዎ መረዳት ምን ማለት እንደሆነ በጥቂቱ ለማብራራት ይሞክሩ።

_______________________________________________
_______________________________________________
_______________________________________________
_______________________________________________
_______________________________________________



የእግዚአብሔር ኃይል በተለያየ መልኩ ተገልጿል። ከነዚህም መካከል አንዱ ሮሜ 1፥20-21 ላይ የተጠቀሰው ነው። እርሱም፥ በፍጥረት ጅማሬ ላይ የተገለጠው፥ የእግዚአብሔር የመፍጠር ኃይል ነው።

በአዲስ ኪዳንም፥ በተመሳሳይ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በተገለጠው ኃይል እንደገና አዲስ ሕይወትን መፍጠሩን ይገልጽልናል(2ኛ ቆሮንቶስ 5፥17)።

አሕዛብ በነበርንበት ጊዜ ሙታን ነበርን። ነገር ግን የወንጌሉ ኃይል ሕያዋን አደረገን። ስለዚህ ጳውሎስ እንደገለጸው ይህ ኃይል ላልዳኑት የግድ የሚያስፈልግ የማዳን ኃይል ነው።

የሰውን ሙት ማንነት በቅጽበት ለውጦ ሕያው የሆነ ማንነት የሚሰጥ እንደ ወንጌል ያለ ምን አይነት ኃይል ይገኛል? "መዳንም በሌላ በማንም የለም …" እንድንበት ዘንድ የተሰጠን የኢየሱስ ስም ብቻ ነው። ይህ ስም የወንጌላችን መሰረት ነው፤ ይህ ስም ብርቱ ኃይል ያለው ታላቅ የማዳን ክንድ ነው።

አ ግሩም ኃይል ነው
አ ግሩም ኃይል ነው
ጌታዬ ሆይ በክንድህ ውስጥ ያለው
አ ግሩም ኃይል ነው!

3. ከሞት ድነን ሕያዋን ለሆንን፥ ወንጌል የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን የሚሆነውስ በምን መልኩ ነው? ወንጌል አስር ጊዜ ሳይሆን እንዴ ነው የሚያድነው። ታድያ ጳውሎስ፥ "ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።" ማለቱ ለምንድን ይመስልዎታል?

_______________________________________________
_______________________________________________
_______________________________________________
_______________________________________________

በቁጥር አስራ ሰባት ላይ ጳውሎስ፥ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።" ሲል በክርስቶስ ውስጥ ሕግን ማርካትና ጽድቅን መፈጸም እንደሚቻል ለመግለጽ ነው።

ወገኖች፥ ዕጣው ተጥሎ ገመዳችን ባማረ ስፍራ ወድቃለች
መስመር ተሻግረን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆነናል
ትናንትናችን ተዋጅቷል ዛሬያችን ተቀድሷል የወደፊት ተስፋችን ጸንቷል
ወደ ኃላ አናይም፣ አናዘግምም፣ አንዘገይም፣ አንቆምም፣ አናፈገፍግም
በአዲስ ኃይል ወደ ፊት እንገሰግሳልን።
አሮጌው ሰው አክትሞለታል፣ አዲሱ ሰው ተነስቷል
የሰነፍ ርምጃ፣ ተራ ወሬ፣ ራዕይ አልባ ሕይወት አበቃ
ከከንቱ ኑሮ ርቀን፣ የተሰጠንን አደራ ለመጠበቅ ተነስተን
ከትተን ተንቀሳቅሰናል፣ ጉዞ ጀምረናል።
ዓላማችን ግልጽ፣ ግባችን አንድ፣ መሪያችን ሁነኛ ነው
በምንም አንገዛም፣ ምንም አናመቻመችም
ፍርሃትና ዕፍረት - በፍቅር ተወግዷል
ጣዕማችን ተለውጦ ምርጫችን ተስተካክሏል
ዝና አንፈልግም፣ ለእድገት አናነፈንፍም
አንደኛ ለመሆን አንጋፋም፣ ለመታየት አንወጣጠርም
በጸሎት እየተደገፍን በትዕግስት እንሮጣለን
የኋላችንን እየረሳን ወደ ፊት እንዘረጋለን
አይኖቻችን ወደ ላይ ሃብታችን በሰማይ
አርማችን ቅድስና መጠሪያችን ሕያዋን
ክብራችን ኢየሱስ፤ ዋጋችንም ኢየሱስ ነው !

4. በጥናታችን ክፍል አራት ውስጥ አይተን ባለፍነው በቁጥር አስራ አምስት ላይ ጳውሎስ፥ “ተዘጋጅቼአለሁ” ሲል በተለይ ከወንጌል ኃይል አኳያ ምን ይመስልዎታል?

## ጽድቅ በእምነት (1፥18-11፥36)

### ኃጢአት - የደህንነት አስፈላጊነት
### 1. ለአሕዛብ (1፥18-2፥16)

እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። (ሮሜ 1፥18-19)



ብዙ ጊዜ እግዚአብሐር በሰዎች ጉዳይ ላይ ምንም ግድ የሌለው የሩቅ አምላክ፥ ወይም ሰው እንደፈለገ ቢሆን ምንም የማይል አሞላቃቂ “ፍቅር” ተደርጎ ሊገመት ይችላል። ከዚህም የተነሳ ሰዎች በተግባራቸውና በአስተሳሰባቸው መረን ሊሆኑ ወይም የእግዚአብሔርን ምክር ሊንቁና ሊያቃልሉ ይችላሉ።

ነገር ግን እግዚአብሔር እያንዳንዱን ፍጡር በቅርበት ስለሚያውቅ፥ የሰው ልጅ ከተቀበለው ከፍተኛ ሃላፊነት የተነሳ ተጠያቂ በመሆኑ ኃላፊነቱን በምን አይነት ሁኔታ በሥራ ላይ እንዳዋለው ዘወትር በትኩረት ይመለከታል። ስለዚህ የማይገባቸውን የሚያደርጉ ሰዎችን እግዚአብሔር በመመልከት ይቆጣል። መልካም በሚያደርጉም ደስ ይሰኛል።

5. በቁጥር 18 በተገለጠው መሠረት የእግዚአብሔር ቁጣ የሚመጣው በማን ላይ ነው? ይህ ቁጣ ምን አይነት ቁጣ ይመስልዎታል? ምንስ ሊመስል ይችላል?

የሰው ቁጣ፥ ንዴት፣ ሥጋት፣ ራስን አለመግዛት፣ ፍርድ አልባነት፣ ቂም፣ ስንፍና፣ ትዕቢትና የመሳሰሉ ኃጢአቶች ያስከትላል። እግዚአብሔር ተቆጣ ስንል ግን፥ ከሰው ቁጣ ጋር ተከትለው የሚመጡት ሁሉ አብረው ከቁጣው ጋር ይመጣሉ ማለታችን አይደለም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቁጣ ውስጥ እነዚህ ነገሮች ሁሉ አይገኙም።

6. በሮሜ 1፥18-21 ድረስ ባለው ክፍል መሰረት፥ ይህ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚመጣባቸው ሰዎች ከተጠያቂነታቸው የሚያመልጡበትን ምክንያት ማቅረብ ይችላሉ? ለምን?

ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ሲነሳ ብዙ ጊዜ ከሚጠየቁት ጥያቄዎች መካከል፥ “ወንጌል ያልተሰበከላቸውና ስለ እግዚአብሔር ምንም የማያውቁ ሰዎችስ?” የሚለው ይገኝበታል።

ጳውሎስ በሮሜ 1፥18-19 ላይ እንደጠቀሰው ማንም ሰው ከተጠያቂነት የሚያመልጥበትን ምክንያት ማቅረብ አይችልም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን እንዲያውቁና እርሱን እንዲያመልኩ ሊያደርጉአቸው የሚችሉ በቂ ምስክሮች በዙሪያቸው ተቀምጠዋል።

7. ታድያ ስለ እግዚአብሔር የሚመሰክሩ ብዙ ነገሮች ካሉ የኛ ምስክርነት ለምን አስፈለገ? ሰዎች ከፍጥረታት ምስክርነት እግዚአብሔር መኖሩን አምነው በጥሩ

ሥነ-ምግባርና አምልኮ (ጧፍ ይዞ በመሄድ፣ ለእግዚአብሔር በመስገድና በመሳሰሉት ተግባራት) መኖር መቻላቸው ከቁጣ ያድናቸው ነበር ማለት ነው? ለምን?

8. በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት በሆኑ ወይም በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ይህ አይነት ቁጣ የሚመጣባቸው ይመስልዎታል? ለምን?

9. ከዛሬው ጥናት የቀረልዎት ወይም ያስተዋሉት ነገር ምንድን ነው?



**ክፍል ስድስት**

# ጽድቅ በእምነት (1፥18-11፥36)

## ኃጢአት - የደህንነት አስፈላጊነት ለአሕዛብ (1፥18-2፥16)

> የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፥ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ። (ሮሜ 1፥ 20-23)

በሐዋርያት ሥራ 14፥17 ላይ እንደተገለጸው። እግዚአብሔር ራሱን ያለምስክር አልተወም። እርሱ እንደ ማንኛውም ሌላ አምላክ በጭፍን ሳይሆን በበቂ መልኩ ራሱን በገለጠው መሰረት የሚመለክ ሕያው አምላክ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ከገለጠባቸው መንገዶች መካከል ዋነኞቹ፥

1. አጠቃላይ መገለጥ (General revelation)
2. ልዩ መገለጥ (Special revelation) በመባል ይታወቃሉ።

በሮሜ 1፥20-21 ላይ ጳውሎስ የሚናገረው ስለ አጠቃላይ መገለጥ (General revelation) ነው።

አጠቃላይ መገለጥ (General revelation) የምንለው እግዚአብሔር በፍጥረታት በኩል ራሱን የገለጠበትን መንገድ ነው።

ለምሳሌ፥ በመዝሙረ ዳዊት 19፥1 ላይ ዘማሪው “ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።” እያለ ፍጥረት ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት እንደሚመሰክሩ ይገልጻል።

በመጽሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ 38 እና 39፣ በመዝሙረ ዳዊት 50፣ በኢሳይያስ 5፥21-22፣ በማቴዎስ 6፥26-32 እና በሮሜ 1፥20 ላይም እንዲሁ በተመሳሳይ ፍጥረታት እግዚአብሔርን በተለያየ መልኩ እንደሚገልጡት ያመለክታሉ።

1. ለመሆኑ ፍጥረታት የእግዚአብሔርን መኖርና ማንነት እንዴት ነው የሚገልጡት?

አጠቃላይ መገለጥ (General revelation) ስለ ደህንነትና ሰለ ክርስቲያን ስነ ምግባር ዝርዝር ገለጻ ባይሰጥም ስለ እግዚአብሔር ጠቅለል ያለ ምስክርነት ይሰጣል። ስለዚህ ሰዎች የፍጥረታትን ብዛት፣ ታላቅነት፣ ክብርና ጠቅላላ አሰራር ሲያዩ ሰሪው ምን ያህል ታላቅና መልካም እንደሆነ መረዳት ይችላሉ።

ምናልባት ስለ ሮቢንሰን ክሩሶ (Robinson Crusoe) ታሪክ ሰምተው ይሆናል። ይህ ሰው መርከበኛ ነበር። አንድ ጊዜ መርከቡ በማዕበል ተመትታ አሸዋማ ደሴት ላይ ተበታተነች። በዚያ ወቅት የሮቢንሰን ክሩሶ ሕይወት ቢተርፍም ማንም ሊደርስለት በማይቻልበት በምድረ በዳ ደሴት ላይ ለብቻው ቀረ። ምንም እንኳን ከዛሬ ነገ መርከብ በደሴቱ በኩል ሲያልፍ ያገኘኛል ብሎ ቢጠባበቅም ብቅ የሚል አንድም መርከብ አልተገኘም ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ሮቢንሰን ክሩሶ በደሴቱ ዳርቻ ላይ ሲሄድ የሰው የእግር ምልክት (ዱካ) አየ። ስለዚህ ቶሎ ብሎ ወደዚያ ወዳየው ዱካ ሄደና በራሱ እግር ለካው። ሆኖም ግን ከራሱ እግር ጋር አልተመጣጠነም ነበር።። ስለዚህ ሮቢንሰን ክሩሶ አንድ ድምዳሜ ላይ ደረሰ። ይኸውም "በደሴቱ ላይ ሌላ ሰው አለ፥ ወይም ነበረ ማለት ነው።" የሚል ድምዳሜ ነበር።

ፍጥረታትም ለሰው ልጆች እግዚአብሔር መኖሩን የሚገልጹት በዚህ መልኩ ነው ማለት ይቻላል። ያንን የሰው እግር ምልክት እያየ ሮቢንሰን ሰው በዚያ ቦታ አልነበረም ለማለት በጣም አስቸጋሪ ሊሆንበት እንደሚችለው ሁሉ፥ አጠቃላይ መገለጥ እያለ መለኮታዊ ኃይል የለም ለማለት በጣም አስቸጋሪ ነው። በነገራችን ላይ፥ እግዚአብሔር መኖሩን ከማመን ይልቅ አለመኖሩን ማመን በጣም ከፍተኛ እምነት ይጠይቃል። ሆኖም ግን በቁጥር ሃያ አንድ ላይ እንደ ተጠቀሰው ሰዎች ልባቸው ስለ ጨለመ ጥልቅ የክህደት አዘቅት ውስጥ ገብተዋል።

አንድ አንድ ጊዜ ለክርስቲያኖች "እንደ አሕዛብ አትሁኑ" ሲባል ምናልባት ፍጥረታትን እያዩ የእግዚአብሔርን መኖር ማየት እንዳልቻሉት አትሁኑ ማለትም ሊሆን ይችላል።

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖችም ብንሆን በዙሪያችን እግዚአብሔር በፍጥረታቱ በኩል መልካምነቱን፣ ታላቅነቱንና አብሮነቱን በግልጽ እያሳየን ግን ላናስተውል እንችላለን።

ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በሥጋ በሚያገለግልበት ጊዜ በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች ይህን "ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ … የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ … ። " በማለት ሰዎች የእግዚአብሔርን እጅ ሥራ እንዲመለከቱ እና በርሱ እንዲያምኑ ያሳስባቸው ነበር።

ወገኖቼ፤ ለብቻችን ያለን በመሰለን ጊዜ ዙሪያችንን እንይ። እግዚአብሔር በጆቹ ሥራ፥ መልካምነቱን፣ ታላቅነቱንና በተለይም ደግሞ አብሮነቱን ጠዋትና ማታ ይነገረናል።

እግዚአብሔር አለ! ከልጅነታችን ጀምሮ አይኖቹ በኛ ላይ ናቸው። አሁንም ያየናል። እርሱ ባጠገባችን ነው። በወፎች ፉጨት ድምጹን ያሰማናል፣ በክዋክብት ድምቀት ክብሩን፣ በነፋሳት ጉልበት ኃይሉን ያሳየናል። የኤልያስ አምላክ ዛሬም ሕያው ሆኖ ባጠገባችን አለ!



2. በቁጥር ሃያ አንድ መሰረት ሰዎች ፍጥረታትን በማየት "አዎ አንድ መለኮታዊ ኃይል እንዳለ አምናለሁ።" ወይም በዩናይትድ ስቴትስ እንደሚባለው በእግዚአብሔር እናምናለን " In God we trust" ማለታቸው በራሱ በቂ ይመስልዎታል? ታዲያ ከዚያ ያለፈ ምን ይጠበቅባቸዋል?

3. በሮሜ 1፥22-23 ላይ አሕዛብን እንዴት ነው የሚገልጻቸው?

በቁጥር ሃያ ሁለት ላይ ደንቆሮ የሚለው ቃል *mōrainō* ከሚለው የተተረጎመ ነው። *mōrainō* ማለት ሞኝ ወይም ዘገምተኛ አዕምሮ ያለው እንደማለት ነው።

ጳውሎስ እንዱ "አላፍርም" ያለበት ምክንያት ምናልባት የአሕዛብን ሁኔታ በእግዚአብሔር እይታ መሰረት ስለተረዳ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ጳውሎስ እንደ ሚናገረው አሕዛብ፥ ምንም እንኳን አዋቂና ጥበበኞች ነን ቢሉም እንኳን ሞኞች ናቸው።

በመዝሙረ ዳዊት 115፥8 ላይ መዝሙረኛው፥ ጣዖታትን ስለሚያመልኩ ሰዎች ሲናገር፥ "የሚሠሩአቸውም የሚያምኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ።" በማለት የጣዖት አምላኪዎችን እጣ ፈንታ ይተነብያል ወይም የሚያመልኩትን ጣዖታት መምሰላቸው የማይቀር መሆኖን ይገልጻል።

በርግጥም ሰው የሚያመልከውን ስለሚመስል፥ ጣዖታትን የሚያመልኩ እንደ ጣዖታቱ፥ ጆሮ አላችው ነገር ግን አይሰሙም፣ አይን አላቸው ነገር ግን አያዩምም። በተጨማሪም እንደ ጣዖታቱ የሚመስሉ እንጂ የሆኑ አይደሉም። ታውረው ሳለ የሚያዩ ይመስላሉ፣ ሕይወት አልባ ሆነው ሳለ የተትረፈረፈ ሕይወት ያላቸው ይመስላሉ።

ጣዖታቱ ባዶ ስም እንደተሸከሙት እነርሱም አለሙን ሁሉ አትርፈው ላያቸው የደመቀ ቢመስሉም እንኳን ውስጣቸው ባዶ ነው፤ ባዶ ክብር፣ ባዶ ዝና ባዶ ስም ነው የያዙት።

ወገኖቼ፤ ታላቅስ እግዚአብሔርን የሚያውቁና የሚፈሩ ናቸው። እግዚአብሔርን የማያውቁና የማይፈሩ በምንም አይነት መጠንና መልክ ትልቅ ቢመስሉም ትንሽ ናቸው። ስለዚህ ምንም ሳናፍር እውርነታቸውን ሊገልጥ የሚችለውን የወንጌል ኃይል በምስክርነታችን ልናቀርብላቸው ይገባናል።

“ … ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን።” (ሮሜ 14፥15)

4. በሮሜ 1፥22-23 ላይ የተጠቀሱት ጣዖታት ምን ምን ናቸው? እንነዚህ የተጠቀሱትን ነገሮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመግለጽ ይሞክሩ።

ሰዎች ጣዖታትን የማምለካቸው ጉዳይ፥

1. የአምልኮ ጥማት እንዳላቸውና
2. ይህን ጥማት በራሳቸው መንገድ ሊያረኩ እንደሚጥሩ ይገልጽልናል።

በዚህ ዘመንም ያለው ሁኔታ እምብዛም የተለየ አይደለም። ሰው ሁሉ አንድ መሰረታዊ ጥማት አለው። ይኸውም የማምለክ ጥማት ነው። ስለዚህ ምንም እንኳን የተለያየ ቅርጽ አስቀምጠው ባያመልኩ፥ የማምለክ ጥማታቸውን በራሳቸው መንገድ ሊያረኩ ይሞክራሉ። ከነዚህም መካከል የሃይማኖት ሥርዓትን ወይም ሃይማኖትን፣ ገንዘብን፣ አገርን፣ ራስንና የመሳሰሉትን ነገሮች ማምለክ ይገኙባቸዋል።

ለምሳሌ ሃይማኖትን ብንመለከት፥ ሰዎች እግዚአብሔርን ሳይሆን የሃይማኖትን ተቋም ሊያመልኩ ይችላሉ። ማለትም ምንም እንኳን እግዚአብሔርን በግል ባያውቁትም፣ በእውነትና በመንፈስ በግል ባያመልኩትም፣ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ባይኖራቸውም፥ በአንድ የሃይማኖት ተቋም ውስጥ በመገኘትና የሃይማኖት ሥርዓቶችን በመፈጸም የማምለክ ጥማታቸውን ለማርካት ይሞክራሉ።

5. አይመስልዎትም?ለምን? (እርስዎ ራስዎ እንዴት ነዎት?)

6. ብዙ ጊዜ ሰዎች ዕውነተኛውን እግዚአብሔርን ያመለክን ወይም እውነተኛውን እግዚአብሔርን የጠራን እየመሰለን፥ ራሳችን ከምንገምተውና ከልማድ ከተረዳነው የሳልነውን እግዚአብሔርን የምንጠራበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። በዚህ ጉዳይ ላይ ምን አስተያየት አለዎት?



ወገኖች፤ እግዚአብሔር ካወቅነው በላይ ትልቅ አምላክ ነው። ከጊዜ አኳያ፣ ከቦታ አኳያ፣ በእውቀትና በአቅም ከምናስበው በላይ በጣም ረቂቅና የተለየ ነው።

እግዚአብሔር ፦

ሁሉን አዋቂ
በሁሉ ስፍራ ባንድ ጊዜ የሚገኝ (ከቦታና ከጊዜ አኳያ)
ሁሉን ማድረግ የሚችል ታላቅ አምላክ ነው።

እግዚአብሔር በሁሉ አቅጣጫ በጣም ታላቅ አምላክ ስለሆነ አውቄ ጨርሼዋለሁ ማለት አንችልም። ስለዚህ ይልቁን በተገለጠልን መጠን በሚገባ እንድናመልከው በየዕለቱ እርሱን በማወቅ ማደግ ያስፈልገናል። አለበለዚያ ጳውሎስ ደንቆሮ (ሞኞች) እንደሚላቸው እንደ አሕዛብ እንሆናለን።

7. እግዚአብሔርን በተገለጠው መጠን አውቀነው በአካሄዳችን ከእርሱ ጋር በሚገባ እንድንመላለስ ምን ማድረግ ያለብን ይመስልዎታል?

8. ከዛሬው ጥናት ምን የቀረልዎት ወይም የተገነዘቡት ነገር አለ? ከዛሬው ጥናት የተነሳ ለራስዎ የነገሩት ወይም ርምጃ ሊወስዱበት ያሰቡት ነገር አለ? ካለ፥ ቢፈልጉ ለቡድንዎ አባላት ይንገሯቸው ወይም የወሰኑትን ውሳኔ ጽፈው ሊያዩት በሚችሉት ቦታ ያስቀምጡት።

# ክፍል ሰባት

ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን። ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ። እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ፥ ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤ እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም። (ሮሜ 1፥24-32)

በክፍል ስድስት ጥናታችን እንዳየነው አሕዛብ በጥልቅ የክህደት አዘቅት ውስጥ ሊገኙ ስለሚችሉ፥ ስለ እግዚአብሔር ማንነት መገንዘብ ይሳናቸዋል። በሮሜ መልእክት እንደምናየው ደግሞ አሕዛብ ልባቸው ሊጨልም ስለሚችል፥ ውጤቱ መጥፎ የሆነ የተሳሳተ ምርጫ አዘውትረው ይመርጣሉ።

1. በሮሜ 1፥24 ላይ አሕዛብ ምን እንደሆኑ ይናገራል? ለምን?

________________________________________

________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

በቁጥር 24 ላይ እንደምናየው ሰው እግዚአብሔርን አለመልክም ብሎ ሲሸሽ ወደ ሕይወቱ ተግተልትለው የሚገቡ ርኩስ ነገሮች መኖራቸው የማይቀር ነው።

2. ብዙ ጊዜ የተለያዩ ምክንያቶች በመስጠት በግልም ሆነ በጋራ ከሚደረግ መንፈሳዊ አምልኮ ራስን ማራቅ፥ ለሚያረክሱ ነገሮች መተውን (ችላ መባልን) ሊያስከትል ይችላል ብለው ያምናሉ? ለምን? (ማንነትን በመቅረጽ አኳያ አምልኮ ምን አይነት ሚና ሊኖረው ይችላል?)

________________________________________

________________________________________



______________________________________________

______________________________________________

ሮሜ 1፥24 ላይ ፥ "ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።" ሲል ካጠፉት ጥፋት የተነሳ በምርጫቸው ሳይሆን በወላጆቻቸው ውሳኔ ለፖሊስ ወይም ለከፋ የጎዳና ሕይወት አልፈው እንደተሰጡ ልጆች አይነት አይደለም። ነገር ግን ምናልባት፥ "ምከረው ምከረው ፥ እንቢ ካለ ተወው ፥ መከራ ይምከረው።" እንደሚሉት አይነት፥ ለመረጡት ሕይወት አልፈው እንደ ተሰጡ አይነት ሰዎች ነው። ስለዚህ አሕዛብ፥ "ውጡልኝ!" በሚል ተገፍትረው ሳይሆን፥ "ካልሄድን!" ብለው የግድ ስለሉ፥ "ይሄው - ሂዱ" በሚል ለመረጡት ርኩሰት ተትተው ነው።

3. አይመስልዎትም? ለምን?

________________________________________

________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

እግዚአብሔር አንፈልግህም ያሉትን ሰዎች በግድ አንቆ ወደ ራሱ አያመጣም። እርሱ በፍቅር ይለምናል እንጂ በጉልበት አያስገድድም። ስለዚህ እንቢ ብለው ክፉ ምኞታቸውን የሙጥኝ ያሉትን፥ ምኞታቸው የሚወልደውን የኃጢአት ፍሬ እንዲበሉ ይተዋቸዋል።

ይህን የሚያደርገው ደግሞ ለመበቀል ሳይሆን፥ ሰው ይበጀኛል ወዳለው ነገር ዘልቆ ገብቶ ሁሉ ከንቱ ወይም የማይረባ መሆኑን ሲረዳ፥ በጊዜ ወደሚበጀው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፥ በጊዜ ወደ እግዚአብሔር ላልተመለሰ ወይም በኃጢአቱ ለቀጠለ ደግሞ የምርጫው ውጤት የመቀበያ መንገድ ሊሆንም ይችላል።

4. በቁጥር ሃያ አራት ላይ እግዚአብሔር አሕዛብን፥ በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት አሳልፎ እንደሰጣቸው ተገልጿል። በዚህ ክፍል ጳውሎስ፥ "ርኩስነት" ሲል ምንን በተመለከተ ይመስልዎታል?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

በብሉይ ኪዳን አለማመንና አለመታመን እንደ መንፈሳዊ ግልሙትና የሚገለጽበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ በሕዝቅኤል 16፥16-26 ላይ፥ የእስራኤል ጣዖታትን ማምለክ እንደ መንፈሳዊ ግልሙትና ሲገለጽ እናያለን።

እንዲያውም፥ በቁጥር ሃያ አምስት ላይ የእስራኤልን ሁኔታ የገለጸው፥ "በየመንገዱ ራስ ክፍ

ያለውን ቦታሽን ሠራሽ፥ ውበትሽንም አረከስሽ፥ ለመንገድ አላፊም ሁሉ እግርሽን ገለጥሽ ግልሙትናሽንም አበዛሽ።" በሚል በጣም አስጸያፊ በሆነ መልኩ ነው።

ይህ አገላለጽ ምንም አይነት ቅርጽና ደረጃ ያላቸው ጣዖታትን ማምለክ በእግዚአብሔር ፊት በጣም ጸያፍ ገጽታ እንዳለው የሚያስገነዝብ ነው።

5. በሮሜ 1፥26-27 ላይ በተገለጸው መሰረት፥ አሕዛብ አልፈው የተሰጡት ለምንድን ነው?

ግብረ ሰዶማዊነት ለመጀመሪያ ጊዜ በዘፍጥረት አስራ ዘጠኝ ላይ የተጠቀሰ ከእግዚአብሔር ሃሳብ ጋር የሚቃረን የኃጢአት ፍሬ የሆነ ከባድ ኃጢአት ነው። እንዲያውም በ1ኛ ቆሮንቶስ 6፥8-10 ላይ፥ ግብረ ሰዶማውያን፥ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም ከተባሉት ርኩስ ተግባራትን ደስ እየተሰኙ ማድረግ ከሚያዘወትሩ ጎራ ውስጥ ተካተው እናገኛቸዋለን። በጣም አሳዛኝና አሳፋሪ ቢሆንም፥ በዝርዝሩ ውስጥ ያሉት ሌሎች ኃጢአቶች በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድም የሚዘወተሩ ናቸው።

6. የግብረ ሰዶማዊነት ባሕሪ የተፈጥሮ ችግር ነው እንጂ ኃጢአት አይደለም ብለው የሚከራረከሩ አሉ። ይህን እንዴት ይመለከቱታል? ግብረ ሰዶማዊነት እንዲሁ በተፈጥሮ የሚመጣ ነገር ይመስልዎታል?

ኃጢአት ሁሉ ገዳይ ነው። ማለትም፥ ማንኛውም ኃጢአት የሚነዳው ወደ ሞት ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ይህን ሃሳብ ሲያጠናክረው፥ "ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።" ይላል። (ያዕቆብ 1፥15)

ግብረ ሰዶማዊነት ምንም እንኳን ከፍተኛ የሞራል መላሸቅ የወለደው ከባድና ጸያፍ ኃጢአት ቢሆንም ከእግዚአብሔር የይቅርታ ክልል ውጭ አይደለም። ስለዚህ ግብረ ሰዶማዊነትን መጥላትና መቃወም የሚገባን ነገር ቢሆንም፥ ግብረ ሰዶማውያንን ግን በፍቅርና በርህራሄ እያየናቸው ልንጸልይላቸውና እጃቸውን ይዘን ከገቡበት የኃጢአት ማጥ ውስጥ ለማውጣት መጣር ያስፈልጋል። አይመስልዎትም?



በሮሜ 1፥28-32 ባለው ክፍል ላይ፥ "እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።" ይላል።

7. ጳውሎስ በዚህ ክፍል በገለጸው መሰረት ይህ የማይረባ አዕምሮ በምን የተሞላ ነው? (በዚህ ክፍል ከተዘረዘሩት አመለካከቶች ውስጥ በእርስዎ አዕምሮ የሚገኝ አለ? ያስቡበት!!)

በሮሜ 1፥28 ላይ እንደ ተገለጸው ሰዎች እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱ ጊዜ፥ ከእግዚአብሔር ሃሳብ ጋር በሚቃረን ሃሳብ ይሞላሉ።

በዘፍጥረት 4፥7 ላይ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሲናገር ፥ "መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።" ይላል።

ክርስቲያን የሆንን እንኳን፥ ምናልባት በአስተሳሰባችንና በድርጊቶቻችን ከእግዚአብሔር ሃሳብ እርቀን የሄድን ከሆነ፥ "አንድ ቀን ድንገት በተዓምር የተሻልን አይነት ሰዎች ሆነን ከመኝታችን እንነሳ ይሆናል።" በሚል መጠበቅ የለብንም። የእግዚአብሔርን ጸጋ ተመርኩዘን በፈቃዳችን ለመለወጥ ካልተጋን በስተቀር እንዲሁ በቀን ብዛትና በዕድሜ መግፋት ልንለወጥ አንችልም። ስለዚህ ማሕበረተኝነታችንን ከሌላ አርገን እግዚአብሔርን በሃሳብና በተግባር የራቅን ካለን ቶሎ በንስሃ ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ያስፈልጋል።

በሮሜ 1፥29-32 ላይ አሕዛብ እግዚአብሔርን ማወቅ ስላልፈለጉና የልባቸውን ክፉ መሻት ስለተከተሉ፥ በተለያዩ ክፉ አስተሳሰቦች እንደተሞሉ ተገልጿል። ይህንን ሁኔታ ጳውሎስ ያቀረበው በሦስት መደቦች ከፋፍሎ ነው ።

1. ኃጢአት በሆኑ ነገሮች መሞላታቸው

   "ዓመፃ ሁሉ፣ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፣ ነፍስ መግደልን፣ ክርክርን፣ ተንኰልን፣ ክፉ ጠባይን ተሞሉ … "

2. ኃጢአተኛ ማንነት መያዛቸው

   " … የሚያሾከሹኩ፣ ሐሜተኞች፣ አምላክን የሚጠሉ፣ የሚያንገላቱ፣ ትዕቢተኞች፣ ትምክህተኞች፣ ክፋትን የሚፈላለጉ፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያስተውሉ፣ ውል የሚያፈርሱ፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ምሕረት ያጡ ሆኑ … "

3. ሴረኞች መሆናቸው

" ... እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።"

**የሰው ቀዳሚ ተፈጥሮ ኃጢአተኛ ማንነት የያዘ አልነበረም። ሰውን ኃጢአተኛ ያደረገው በምርጫው ፊቱን ከእግዚአብሔር በማዞሩ ምክንያት ከተሞላው ኃጢአታዊ አስተሳሰብ ነው። ለምሳሌ አንድ ኮምፒውተር ኦፕሬቲንግ ሲስተሙ 'ዊንዶ ሰቨን' ነው የሚባለው በውስጡ 'የዊንዶ ሰቨን ሶፍት ዌር' ሲጫንበት (ሲሞላበት) ነው። በተመሳሳይ ሰው የተሞላውን ነገር እየሆነ ሊመጣ ስለሚችል፥ ኃጢአት በሆኑ ነገሮች የተሞላም ኃጢአተኛ የሆነ ማንነት ይይዛል።**

**ሌላው ደግሞ አንዳንድ ተመሳሳይነት ያላቸው ሰዎች ሊፈላለጉ ወይም ሊሳሳቡ እንደሚችሉ ኃጢአተኛ ሰውም መሰሉን ሊፈልግ ይችላል።**

8. ከዛሬው ጥናት የቀረልዎት ወይም የተገነዘቡት ነገር ምንድን ነው?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________



**ክፍል ስምንት**

# ጽድቅ በእምነት (ሮሜ1፥18-11፥36)

## ኃጢአት - የደህንነት አስፈላጊነት

## ለአሕዛብ (1፥18-2፥16)

ስለዚህ፥ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና። እንደዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን። አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ፥ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን? ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምሥጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል። ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤ ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምሥጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፥ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው። እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና። ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና። ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። ይህም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ በሰው ዘንድ የተሰወረውን በሚፈርድበት ቀን ይሆናል። (ሮሜ 2፥1-16)

**ይህ መልእክት የተጻፈው በሮም ይገኙ ለነበሩ አማኝ አሕዛብ ቢሆንም እንኳን ፣ አይሁድንም እንደሚመለከት ጳውሎስ ጠቅሷል። አይሁዶች በእግዚአብሔር የሚያምኑ ናቸው፥ ነገር ግን ባህልና ሥርዓት እንደ ቅርፊት በላያቸው ስለተጋገረ፥ እውነትን መገንዘብ ተስኗቸዋል።**

**በሮሜ 1፥18-2፥16 ያለው ክፍል፥ በእግዚአብሔር የማያምኑ አሕዛብን የተመለከተ ቢሆንም እንኳን በእግዚአብሔር መቅደስ እየተመላለሱ እግዚአብሔርን ማየት የተሳናቸውንም ሊያካትት ይችላል። ይህ ደግሞ በዚህም ዘመን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያለነው ሁሉ፥ ራሳችንን ፈትሸን እንደሚገባ መሆን እንዳለብን ያሳስበናል።**

**የሮሜ መልእክት ሁለተኛ ምዕራፍ የሚጀምረው፥ "ስለዚህ" በሚል ቃል ነው። ይህ ቃል አሁን ሊገለጽ ያለውን ሃሳብ ከቀደመው ሃሳብ ጋር የሚያያይዝ ስለሆነ፥ በምዕራፍ ሁለት**

የሚገለጸው ሃሳብ በምዕራፍ አንድ ከቁጥር አስራ ስምንት ጀምሮ የተገለጸው ሃሳብ ቀጣይ መሆኑን ያስገነዝበናል።

1. በሮሜ 2፥1 ላይ ጳውሎስ ምን ይላል? ለምን አይነት ሰው የተባለ ቃል ነው?

ጳውሎስ በዚህ የመልእክቱ ክፍል ላይ የገለጸው ጉዳይ፥ የኬጢያዊውንም የኦርዮንን ሚስት ቤርሳቤህን የራሱ ለማድረግ የፈጸመውን የዳዊትን ስውር ደባ ያስታውሰናል። ዳዊት በቤተ መንግስቱ ሰገነት ላይ ሳለ አይቶ የተመኛትን የኦርዮንን ሚስት ቤርሳቤህን ከደፈራት በኋላ የራሱ ለማድረግ በጥንቃቄ የወጠነው ሥውር ደባ ነበረው።

የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነው ነቢዩ ናታን ደግሞ የዳዊትን ሥውር በደል በምሳሌ አድርጎ ለዳዊት ለራሱ ነግሮት ነበር። ዳዊትም በሰማው ታሪክ በጣም ስለተቆጣ፥ ይህን ባደረገው ሰው ላይ የፍርድ ቃል ሲናገር፥ የእግዚአብሔር ሰው ነቢዩ ናታን በደለኛው ራሱ ዳዊት መሆኑን፥ “ያ ሰው አንተ ነህ።” በማለት ገልጾለት ነበር።

2. ጳውሎስ በሮሜ 2፥1 ላይ የገለጸው ሃሳብና በ2ኛ ነገስት 11፥1-12፥7 ላይ የሰፈረው ታሪክ፥ በሮም ስለሚገኙ ወገኖች ምን ያስገነዝበናል? በዚህ ዘመን ላለን ለኛስ?

ጳውሎስ ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ ስለ አሕዛብ ኃጢአትና ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ሲናገር፥ ክርስቲያን የሆኑትን ጨምሮ አይሁድ የሆኑ አድማጮቹ፥ “አዎ - ልክ ነው!” በሚል የፈራጅነት ስሜት መልእክቱን እየተቀበሉ ሊሆን ይችላል።

“እግዚአብሔር … ወደ ርኩሰት አሳልፎ ሰጣቸው።” ሲባል፥
“ይገባቸዋል!” ብለው ይሆናል።
“ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው።” ሲባልም፥
“ልክ ነው - ይገባቸዋል!” ብለው ይሆናል።
“እግዚአብሔር … ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።” ሲባል፥
“ ኧረ ይስጣቸው! ከዚህም የከፋ ቢሆኑ ይገባቸዋል!” ብለው ይሆናል።
“አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም።” (እናንተም የምታመካኙበት የላችሁም።) ሲባሉ ግን ምናልባት ጸጥታ ሊሰፍን ይችላል።



ከዚያም፥ “ምን ማለቱ ነው?” የሚል ድንጋጤን፣ ቁጣንና ግራ መጋባትን ያዘለ ጥያቄ፥ አንዱ ለሌላው በሹክሹክታ ሊያነሳ ይችላል።

ሆኖም ግን ጳውሎስ በድፍረት፥ “በሌላው በምትፈርድበት ነገር ግን ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና።” እያለ ያሳስባቸዋል።

ይህ አገላለጽ፥ ናታን የዳዊትን ሥውር በደል ገላልጦ ባሳየው ጊዜ ዳዊት የሚያመካኘው አጥቶ ክው እንዳለ ሁሉ፥ አይሁዳዊ የሮሜ ቤተ ክርስቲያን አድማጮችንም ምክንያት አጥተው በድንጋጤ ለንስሐ እንዲደፉ ሊያደርግ የሚችል ነበር።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ያለን፥ የሌሎችን ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የምንኮንን፥ በግብረ ሰዶማውያን ላይ የምንፈርድ (መፍረድ ሲባል መቃወምን አያካትትም)፣ በሉቃስ 18፥10-14 ላይ እንደ ተጠቀሰው ፈሪሳዊ፥ ራሳችንን ከሌላው እንደ ተሻለ አድርገን የምንቆጥር፥ የሌሎችን ጉድፍ እያየን የምንፈርድ ካለን፥ አስቀድመን ራሳችንን በክርስቶስ ቃል እየፈተሸን በዓይናችን ያለውን ምሰሶ እንድናወጣ ያስፈልጋል። በሰው ከመፍረድ ይልቅ እንደ ቀራጩ እግዚአብሔር ፊት በራስ መፍረድ የተሻለ ነው።

በሮሜ 2፥1 ላይ፥ “ … የምታመካኘው የለህም።” የሚለው ቃል አንድ ሰው በሰራው ጥፋት ተከሶ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ወይም ጉዳዩ አይመለከተኝም ለማለት የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሲገኝ በፍርድ ቤት አካባቢ በሥራ ላይ የሚውል አባባል እንደሆነ ይነገራል።

ስለዚህ በሰው ላይ የመጨረሻውን የፍርድ ቃል የሚናገረው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሰው ሁሉ ግን በፊቱ ዝም ይላል። ጉዳዩን ሊያሳምርለት የሚያስችል ምንም አይነት ምክንያት ማቅረብ የሚችል ማንም ሰው የለም። ስለዚህ “እኔ ጽድቄ ብዬ የምለው እንኳን በፊትህ እንደ መርገም ጨርቅ ነውና ጌታ ሆይ እባክህ በምሕረትህ አሰበኝ!” ማለቱ ይበጃል።

ይህ ሲባል ታዲያ የኃጢአተኞችን ርኩሰት መጸየፍ ወይም መግለጥ የለብንም ማለት ሳይሆን፥ ምናልባት እኛ ራሳችን ከነርሱ ያልተሻልን ከሆንን (በልባችን የምናመነዝር፣ የምንጠላ፣ ተንኮልና ክፉ ጠባይ የተሞላን ከሆንን) እጃችንን እየጠቆምን መፍረዱን ትተን መጀመሪያ ራሳችንን በመፈተሽ በንሰሐ እንስተካከል፣ ራሳችንንም ዝቅ አድርገን በእግዚአብሔር ፊት በትሕትና እንመላለስ ለማለት ነው።

3. በቁጥር ሁለት ላይ፥ “… እንደዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን።” ሲል ማንን በተመለከተ ነው? ምንስ ማለቱ ነው?

በሮሜ 2፥3-5 ባለው ክፍል ጳውሎስ አሁንም በራሳቸው ያለውን ምሰሶ ሳያዩ በሌሎች

ላይ ያለውን ጉድፍ በማየት የሚሳለቁና የፍርድ ቃል የሚናገሩ አይሁዶች ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ ካስታወቀ በኋላ፥ የእግዚአብሔር ቁጣ በአሕዛብ እንደ ተገለጠ በእነርሱ ላይ ግን ያልተገለጠበት ምክንያት ምን እንደሆነ ይገልጻል።

4. ምክንያቱ ምንድን ነው?

ፈራጅ ሰው፥ ምናልባት የራሱን ድካምና የጌታን ጸጋ በሙላት መረዳት የተሳነው ሊሆን ይችላል። የራሱን ድካም ሸፍኖ በደነደነ ልብ መፍረዱን የሚቀጥል ደግሞ የእግዚአብሔርን ቁጣ በራሱ ላይ እንደሚያከማች ጳውሎስ በመልእክቱ ላይ ይገልጻል።

5. ይሄ ቁጣ መቼ የሚገለጥ ይመስልዎታል? ምን አይነትስ ቁጣ እንደሆነ ያስባሉ?

ዛሬ ብዙዎቻችን እግዚአብሔር በልጁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለንሰሐ እድል ስለሰጠንና ስለታገሰን እንጂ፥ ምናልባት ከሰው እይታ የተሰወሩ፥ ለእግዚአብሔር ግን የተገለጡ ብዙ ጸያፍ ተግባሮችና አስተሳሰቦች ይኖሩን ይሆናል። ስለዚህ ጌታን ስለብዙ ትዕግስቱና ቸርነቱ እያመሰገንን በጸጋው ብዛት የበደላችንን ብዛት እንዲሸፍንልን በንሰሐ ዘወትር በፊቱ ልንቀርብ ይገባናል።

6. ሮሜ 2፥5-8 ላይ ያለውን ክፍል ስናነብ በቁጣው ቀን ማለትም የእግዚአብሔር ፍርድ በሚገለጥበት ቀን ሁሉም ሰው፥ "እንደ ሥራው" እንደሚከፈለው ተገልጿል። (ተጨማሪ ንባብ፦ ዮሐንስ 5፥28-29፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥10) ታዲያ ይህ ሃሳብ በሮሜ 3፥24 ላይ ከተገለጸው፥ "ደህንነት እንዲሁ በጸጋ የሚገኝ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው።" ከሚለው ሃሳብ ጋር የሚቃረን ይመስላል? እርስዎ እነዚህን ተቃራኒ የሚመስሉ ሁሉት አሳቦች እንዴት ያስታርቁአቸዋል?

በሮሜ 2፥6-7 ላይ፥ "በጎ ሥራ" ሲባል ከልብ ዝንባሌ የመነጨ በጎ ተግባርን የሚመለከት



ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰውን ውጫዊ ድርጊት ሳይሆን ውስጣዊ መነሻ (Motive) ይመረምራል። (ምሳሌ 24፥12)

በቁጥር ሰባት ላይ የተጠቀሰው፥ "በመጽናት" የሚለው ቃል፥ በጎ የሆነውን ሥራ የሚቃወም ክፉ አሰራር መኖሩን ያመለክታል። ስለዚህ በክርስቶስ የተወሰነውን ብድራት ፊት ለፊት እያዩ በበጎ ሥራ መጽናት እንደሚያስፈልግ ያሳስባል።

7. በሮሜ 2፥ 8-11 ድረስ ያለውን ክፍል ስናነብ በምናገኘው ሃሳብ ውስጥ፥ " … በአይሁድ ከዚያም በአሕዛብ … " የሚል ቃል ተጠቅሷል። ይህ ቃል ምን ይገልጽልናል?

8. በሮሜ 2፥12-15 ላይ ያለውን ሃሳብ እንዴት ተረዱት? እስቲ በዚህ ክፍል የተጠቀሰውን ሃሳብ በራስዎ አባባል ለመግለጽ ይሞክሩ?

9. ከዛሬው ጥናት የቀረልዎት ወይም የተገነዘቡት ነገር ካለ ለቡድንዎ ያካፍሉ።